በመደበቁ ምክንያት በእስራኤል ሕዝብ ላይ
መቅሠፍት አምጥቶ ነበር ።
8 ኤታንም ዐዛርያ የተባለ አንድ ወንድ ልጅ
ወለደ ።

### የንጉሥ ዳዊት የትውልድ ሐረግ

9 ሔጽሮን ሦስት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤
እነርሱም ይራሕምኤል ፥ ራምና ካሌብ ተብ
ለው የሚጠሩ ናቸው ፤ 10 ከራም እስከ እሴይ
ያለው የትውልድ ሐረግም ራም ፥ ዓሚናዳብ ፥
ከይሁዳ ነገድ ታዋቂ የሆነው ነአሶን ፥ 11 ሳል
ሞን ፥ ቦዔዝ ፥ 12 ኢዮቤድና እሴይ ነው ።
13 እሴይ ሰባት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ እነር
ሱም እንደ ዕድሜአቸው ቅደም ተከተል ኤሊ
አብ ፥ አሚናዳብ ፥ ሺማ ፥ 14 ናትናኤል ፥
ራዳይ ፥ 15 ኦጼምና ዳዊት ናቸው ። 16 እሴይ
ጽሩያና አቢጋይል ተብለው የሚጠሩ ሁለት
ሴቶች ልጆችንም ወለደ ።
የእሴይ ልጅ ጽሩያ ሦስት ወንዶች ልጆችን
ወለደች ፤ እነርሱም አቢሳይ ፥ ኢዮአብና ዐሣ
ሄል ተብለው የሚጠሩ ናቸው ፤ 17 ሌላይቱ የእ
ሴይ ሴት ልጅ አቢጋይል የእስማኤል ዝርያ የሆ
ነውን ዬቴርን አግብታ ዐማሳ ተብሎ የሚጠራ
ውን ወንድ ልጅ ወለደች ።

### የሔጽሮን ዝርያዎች

18 የሔጽሮን ልጅ ካሌብ ዐዙባ የተባለች
ሴት አግብቶ ይሪዖት ተብላ የምትጠራ ሴት
ልጅ ወለደ ፤ ይሪዖትም ዬሼር ፥ ሾባብና አርዶን
ተብለው የሚጠሩ ሦስት ወንዶች ልጆችን ወለ
ደች ። 19 ዐዙባ ከሞተችም በኋላ ካሌብ ኤፍ
ራታ ተብላ የምትጠራ ሴት አግብቶ ሑር
ተብሎ የሚጠራ ወንድ ልጅ ወለደ ፤ 20 ሑርም
ኡሪ የተባለውን ወንድ ልጅ ወለደ ፤ ኡሪም ባጽ
ልኤል ተብሎ የሚጠራውን ወንድ ልጅ
ወለደ ።
21 ሔጽሮን ስልሳ ዓመት ሲሞላው የገለዓድ
አባት የነበረችውን የማኪርን ልጅ አግብቶ
ሰጉብ የተባለውን ወንድ ልጅ ወለደ ፤ 22 ሰጉ
ብም ያኢር ተብሎ የሚጠራውን ወንድ ልጅ
ወለደ ፤ ያኢር በገለዓድ ግዛት ውስጥ የሚገኙ
ትን ሃያ ሦስት ከተማዎች ያስተዳድር ነበር ፤
23 ነገር ግን የገሹርና የአራም ነገሥታት ስልሳ
የሚያህሉ ታናናሽ ከተማዎችን ከዚያው ከገለ
ዓድ ድል አድርጎ ያዘ ፤ ይህም የያኢርንና የቀና
ትን መንደሮች እንዲሁም በአቅራቢያቸው ያሉ
ትንም ታናናሽ ከተማዎች የሚያጠቃልል
ነበር ፤ በዚያ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የገለዓድ
አባት የማኪር ዝርያዎች ናቸው ፤ 24 ሔጽሮን
በካሌብ ኤፍራታ ከሞተ በኋላ አቢያ ከተባለ
ችው ሚስቱ አሽሑር ተብሎ የሚጠራውን
ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ አሽሑር ተቆዓ ተብላ
የምትጠራውን ከተማ ቆረቆረ ።

### የይራሕመኤል ዝርያዎች

25 የሔጽሮን የበኵር ልጅ ይራሕመኤል አም
ስት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ እነርሱም የመጀ
መሪያው ራም ቀጥሎም ቡና ፥ ኦሬን ፥ ኦጼምና
አሒያ ተብለው የሚጠሩ ነበሩ ፤ 26-27 ራም
ሦስት ወንድ ልጆችን ወለደ ፤ እነርሱም
ማዓጽ ፥ ያሚንና ዔቄር ተብለው የሚጠሩ
ናቸው ፤ ይራሕመኤል ፥ ዐታራ ተብላ የምት
ጠራ አንዲት ሌላ ሴት አግብቶ ኦናም ተብሎ
የሚጠራ ወንድ ልጅ ወለደ ፤ 28 ኦናምም ሻማ
ይና ያዳዕ የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ፤ ሻማይም ናዳብና አቢሹር የተባሉ
ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ ።
29 አቢሹርም አቢኃይል ተብላ የምትጠራ
አንዲት ሴት አግብቶ አሕባንና ሞሊድ ተብለው
የሚጠሩ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ 30 የአ
ቢሹር ወንድም ናዳብ ሴሌድና አፋይም የተ
ባሉ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ ሴሌድ
ግን አንድም ወንድ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ።
31 አፋይምም ዩሺዒ የተባለውን ወንድ ልጅ
ወለደ ፤ ዩሺዒም ሼሻን የተባለውን ወንድ ልጅ
ወለደ ። ሼሻንም አሕላይ የተባለውን ወንድ
ልጅ ወለደ ።
32 የሻማይ ወንድም ያዳዕ ዬቴርና ዮናታን
ተብለው የሚጠሩ ሁለት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ፤ ዬቴር ግን አንድም ወንድ ልጅ ሳይወ
ልድ ሞተ ፤ 33 ዮናታንም ፔሌትና ዛዛ የተባሉ
ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ እነዚህ ሁሉ
የይራሕመኤል ዝርያዎች ናቸው ።
34 ሼሻን ከሴቶች በቀር ወንዶች ልጆች አል
ነበሩትም ፤ እርሱም ያርሐዕ ተብሎ የሚጠራ
አንድ ግብጻዊ አገልጋይ ነበረው ፤ 35 ለዚህም
ለአገልጋዩ ከሴቶች ልጆቹ አንዲቱን ዳረለት ፤
ያርሐዕምም ዓታይ ተብሎ የሚጠራ አንድ
ወንድ ልጅ ወለደ ፤ 36 ከዓታይ እስከ ኤሊሻማዕ
ያለው የትውልድ ሐረግ ፥ ኢታይ ፥ ናታን ፥
ዛባድ ፥ 37 ኤፍላል ፥ ዖቤድ ፥ 38 ዬሁ ፥ ዐዛርያ ፥
39 ሔሌጽ ፥ ኤልዓሳ ፥ 40 ሲስማይ ፥ ሻሉም ፥
41 ይቃምያና ኤሊሻማዕ ነው ።

### ሌሎቹ የካሌብ ዝርያዎች

42 የይራሕመኤል ወንድም የነበረው የካሌብ
በኵር ልጅ ስሙ ሜሻዕ ይባል ነበር ፤ ይህም
ሜሻዕ ዚፍ ተብሎ የሚጠራውን ወንድ ልጅ
ወለደ ፤ ዚፍም ማሬሻን ወለደ ፤ ማሬሻም ኬብ
ሮንን ወለደ ፤ 43 ኬብሮንም ቆራሕ ፥ ታፑሐ ፥
ሬቄምና ሼማዕ ተብለው የሚጠሩትን አራት
ወንዶች ልጆችን ወለደ ። 44 ሼማዕም ራሐምን
ወለደ ፤ ራሐምም ዮርቀዓምን ወለደ ፤ የሼማዕ
ወንድም ሬቄም ሻማይን ወለደ ፤ 45 ሻማይም
ማዖንን ወለደ ፤ ማዖንም ቤትጹርን ወለደ ።

## ምዕራፍ 8

### የብንያም ዝርያዎች

1 ብንያም አምስት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤
እነርሱም በየዕድሜአቸው ተራ ፥ ቤላዕ ፥ አሽ
ቤል ፥ አሕራሕ ፥ 2 ኖሐና ፥ ራፋ ተብለው የሚ
ጠሩት ናቸው ።
3 የቤላዕ ዝርያዎች አዳር ፥ ጌራ ፥ አቢሁድ ፥
4 አቢሹዓ ፥ ናዕማን ፥ አሖሐ ፥ 5 ጌራ ፥ ሽፉፋ
ንና ሑራም ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።
6-7 የኤሁድ ዝርያዎች ናዕማን ፥ አሒያና
ጌራ ተብለው የሚጠሩት ናቸው ፤ እነርሱም
በጌባዕ ይኖሩ ለነበሩት በኋላ ግን ከዚያ ተባር
ረው ወደ ማናሐት ሄደው በዚያ ለኖሩ ቤተሰ
ቦች አለቆች ነበሩ ፤ ወደዚያም የመራቸው የዑ
ዛና የአሒሑድ አባት ጌራ ነበር ።
8-9 ሻሐራም ፥ ሑሺምና ባዕራ ተብለው የሚ
ጠሩትን ሁለት ሚስቶቹን ፈታ ፤ ዘግየት ብሎም
በሞአብ አገር ሲኖር ሖዴሽ ተብላ የምትጠራ
አንዲት ሴት አግብቶ ሰባት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ፤ እነርሱም ዮባብ ፥ ጺብያ ፥ ሜሻ ፥ ማል
ካም ፥ 10 የዑጽ ፥ ሳክያና ሚርማ ተብለው የሚ
ጠሩት ናቸው ፤ የእርሱ ወንዶች ልጆች በሙሉ
የቤተሰብ አለቆች ሆኑ ።
11 በተጨማሪም ሑሺም ከተባለችው ሚስቱ
አሂቱብና ኤልፓዓል ተብለው የሚጠሩ ሁለት
ወንዶች ልጆችን ወለደ ።
12 ኤልፓዓልም ዔቤር ፥ ሚሽዓምና ሼሜድ
ተብለው የሚጠሩ ሦስት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ፤ ሼሜድም ኦኖና ሎድ ተብለው የሚጠ
ሩትን ከተማዎችና በዙሪያቸው የሚገኙትን
መንደሮች የሠራ ነው ።

### በጋትና በአያሎን ይኖሩ የነበሩ ብንያማውያን

13 በሪዓና ሼማዕ በአያሎን ከተማ ለሰፈሩት
ቤተሰቦች አለቆች ነበሩ ፤ እነርሱም በጋት
ከተማ የሚኖሩትን ሕዝብ አባረሩ ፤ 14 የበሪዓ
ዝርያዎች አሕዮ ፥ ሻሻቅ ፥ ይሬሞት ፥ 15 ዘባ
ድያ ፥ ዐራድ ፥ ዔዴር ፥ 16 ሚካኤል ፥ ዩሽፓና
ዮሐ ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።

### በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ብንያማውያን

17 የኤልፓዓል ዝርያዎች ዘባድያ ፥ መሹ
ላም ፥ ሒዝቂ ፥ ሔቤር ፥ 18 ዩሽመራይ ፥ ዩዝሊ
አና ዮባብ ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።
19 የሺምዒ ዝርያዎች ያቂም ፥ ዚክሪ ፥
ዛብዲ ፥ 20 ኤሊዔናይ ፥ ጺልታይ ፥ ኤሊኤል ፥
21 ዐዳያ ፥ በራያና ሺምራት ተብለው የሚጠሩት
ናቸው ።
22 የሻሻቅ ዝርያዎች ዩሽን ፥ ዔቤር ፥ ኤሊ
ኤል ፥ 23 ዓብዶን ፥ ዚክሪ ፥ ሐናን ፥ 24 ሐና
ንያ ፥ ዔላም ፥ ዓንቶቲያ ፥ 25 ዩፍደያና ፋኑኤል
ተብለው የሚጠሩ ናቸው ።
26 የይሮሐም ዝርያዎች ሻምሽራይ ፥ ሸሐ
ርያ ፥ ዐታልያ ፥ 27 ያዕሬሽያ ፥ ኤሊያና ዚክሪ
ተብለው የሚጠሩት ናቸው ።
28 እነዚህ ሁሉ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ለነበ
ሩት ቀደም ያሉ የቤተሰብ አለቆችና የእነርሱም
ዋና ዋና ዝርያዎች ናቸው ።

### በገባዖንና በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ብንያማውያን

29 ይዒኤል የገባዖንን ከተማ ቆርቁሮ በዚ
ያው ኖረ ፤ ሚስቱ ማዕካ ተብላ የምትጠራ ስት
ሆን ፥ 30 የበኵር ልጁም ዓብዶን ይባል ነበር ፤
ሌሎቹ የእርሱ ወንዶች ልጆች ጹር ፥ ቂሽ ፥
ባዓል ፥ ኔር ፥ ናዳብ ፥ 31 ገዶር ፥ አሕዮ ፥ ዜኬ
ርና ፥ 32 የሺምዓ አባት ሚቅሎት ተብለው የሚ
ጠሩት ናቸው ፤ የእነርሱም ዝርያዎች በሌሎቹ
የጎሳቸው ቤተሰቦች አቅራቢያ በኢየሩሳሌም
ይኖሩ ነበር ።

### የንጉሥ ሳኦል ቤተሰብ

33 ኔር ቂስን ወለደ ፤ ቂስ ንጉሥ ሳኦልን
ወለደ ፤ ሳኦልም ዮናታን ፥ ማልኪሹዓ ፥ አቢናዳ
ብና ኤሽባዓል ተብለው የሚጠሩትን አራት ወን
ዶች ልጆችን ወለደ ፤ 34 ዮናታንም መሪባዓልን
ወለደ ፤ መሪባዓልም ሚካን ወለደ ።
35 ሚካም ፒቶን ፥ ሜሌክ ፥ ታሬዓና አሐዝ
ተብለው የሚጠሩትን አራት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ። 36 አሐዝ የሆዓዳን ወለደ ፤ የሆዓዳም
ዓሌሜት ፥ ዓዝማዌትና ዚምሪ ተብለው የሚጠ
ሩትን ሦስት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ ዚምሪም
ሞጻን ወለደ ፤ 37 ሞጻም ቢንዓን ወለደ ፤ ቢንዓ
ራፋን ወለደ ፤ ራፋ ኤልዓሳን ወለደ ፤ ኤልዓሳም
አጼልን ወለደ ።
38 አጼልም ዓዝሪቃም ፥ ቦክሩ ፥ እስማኤል ፥
ሸዓርያ ፥ ዖባድያና ሐናን ተብለው የሚጠሩትን
ስድስት ወንዶች ልጆችን ወለደ ፤ 39 የአጼል
ወንድም ዔሼቅም ኡላም ፥ ያዑሽና ኤሊፌሌጥ
ተብለው የሚጠሩ ሦስት ወንዶች ልጆችን
ወለደ ።
40 የኡላም ወንዶች ልጆች ዝነኛ ወታደሮ
ችና ቀስት ወርዋሪዎች ነበሩ ፤ የእነርሱም ዝር
ያዎች በአጠቃላይ አንድ መቶ ኀምሳ ልጆችና
የልጅ ልጆች ነበሩ ፤ እንግዲህ ከዚህ በላይ ስሞ
ቻቸው የተጠቀሱት ሁሉ የብንያም ነገድ ዝርያ
ዎች ነበሩ ።

## ምዕራፍ 9

### ከምርኮ የተመለሰው የእስራኤል ሕዝብ

1 የእስራኤል ሕዝብ በየቤተሰባቸው ተመዝግ
በው ነበር ፤ ይህም ታሪክ በእስራኤል ነገሥታት
መጽሐፍ ሰፍሮ ይገኛል ።
የይሁዳ ሕዝብ በሠሩት ኃጢአት ምክንያት
በመቀጣት ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰደው

መቅደሱ የሚገቡትን የቅጽር በሮች መጠበቃቸ
ውን ቀጠሉ። 24 በእያንዳንዱ አቅጣጫ ማለ
ትም በሰሜን፥ በደቡብ፥ በምሥራቅና በምዕ
ራብ ፊት ለፊት አንዳንድ ቅጽር በር ነበር፤
በእያንዳንዱም ቅጽር በር አንድ የዘበኞች አለቃ
ነበር፤ 25 እነዚህን ዘበኞች በመንደሮቻቸው
የሚኖሩ ዘመዶቻቸው በየሰባቱ ቀን ተራ እየ
ገቡ መርዳት ነበረባቸው፤ 26 አራቱም ሌዋው
ያን የዘበኞች አለቆች ሲሆኑ እነርሱም ሙሉ
ሥልጣን ያላቸው ነበሩ፤ እንዲሁም በቤተ
መቅደሱ ላሉት ክፍሎችና በውስጣቸውም ለሚ
ቀመጡ ዕቃዎች ኀላፊዎች ነበሩ። 27 ቤተ
መቅደሱን የመጠበቅና በየማለዳው የቅጽር በሮ
ችን የመክፈት ተግባር የእነርሱ በመሆኑ እነ
ርሱ የሚያድሩት በቤተ መቅደሱ አካባቢ
ነበር።

### ሌሎች ሌዋውያን

28 ሌሎቹ ሌዋውያን በአምልኮ ጊዜ መገል
ገያ ለሆኑ ንዋያተ ቅድሳት ኀላፊዎች ነበሩ፤
በአገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ እየቈጠሩ
አውጥተው፥ አገልግሎታቸው ሲያበቃም እየቈ
ጠሩ መልሰው ያስቀምጡአቸው ነበር። 29 የቀ
ሩት ሌዋውያን ደግሞ ለሌሎቹ ንዋያተ ቅድ
ሳት፥ ለዱቄቱ፥ ለወይን ጠጁ፥ ለወይራ
ዘይቱ፥ ለዕጣንና ለልዩ ልዩ ቅመማቅመም
ሁሉ ኀላፊዎች ነበሩ፤ 30 ቅመማቅመሙን የመ
ለወሱ ኀላፊነት ግን የካህናቱ ብቻ ነበር።
31 ከቆሬሕ ጐሳ የሻሉም የበኵር ልጅ የሆ
ነው ማቲትያ የመባውን ኅብስት የማዘጋጀት
ኀላፊነት ነበረው፤ 32 የቀሃት ጐሳ አባሎች
ለቤተ መቅደስ የሚሆን ኅብስት በየሰንበቱ የማ
ዘጋጀት ኀላፊነት ነበረባቸው።
33 ከሌዋውያን ቤተሰቦች ከፊሉ ደግሞ
በቤተ መቅደስ የመዘመር ኀላፊነት ነበረባ
ቸው፤ የእነዚህ ቤተሰቦች አለቆች ቀንና ሌሊት
በሥራ ላይ ስለሚገኙ በቤተ መቅደሱ ቅጽር
ግቢ ባሉት ቤቶች ውስጥ ይኖሩ ነበር፤ ከሌ
ሎች አገልግሎቶችም ነጻ ነበሩ።
34 ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉ በቀድሞ
አባቶቻቸው የትውልድ ሐረግ መሠረት የሌዋ
ውያን ቤተሰቦች አለቆች ሲሆኑ የሚኖሩትም
በኢየሩሳሌም ነበር።

### የንጉሥ ሳኦል የቀድሞ አባቶችና ዝርያዎች
(1 ዜ.መ. 8፥29-38)

35 ይዒኤል የገባዖንን ከተማ ቈርቈሮ በዚ
ያው ኖረ፤ ሚስቱ ማዕካ ተብላ የምትጠራ ስት
ሆን፥ 36 የበኵር ልጁም ዓብዶን ይባል ነበር፤
ሌሎቹ የእርሱ ወንዶች ልጆች ጹር፥ ቂሽ፥
ባዓል፥ ኔር፥ ናዳብ፥ 37 ገዶር፥ አሒዮ፥ ዘካሪ
ያና የሺምዓ አባት ሚቅሎት ተብለው የሚጠ
ሩት ናቸው፤ 38 የእነርሱም ዝርያዎች በሌሎቹ
የጐሳቸው ቤተሰቦች አቅራቢያ በኢየሩሳሌም
ይኖሩ ነበር።
39 ኔር ቂስን ወለደ፤ ቂስ ንጉሥ ሳኦልን
ወለደ፤ ሳኦልም ዮናታን፥ ማልኪሹዓ፥ አቢናዳ
ብና ኤሽባዓል ተብለው የሚጠሩትን አራት ወን
ዶች ልጆችን ወለደ፤ 40 ዮናታንም መሪባዓልን
ወለደ፤ መሪባዓልም ሚካን ወለደ፤ 41 ሚካም
ፒቶን፥ ሜሌክ፥ ታሬዓና አሐዝ ተብለው የሚ
ጠሩትን አራት ወንዶች ልጆችን ወለደ፤
42 አሐዝም ያዕራን ወለደ፤ ያዕራም ዓሌሜት፥
ዓዝማዌትና ዚምሪ ተብለው የሚጠሩትን ሦስት
ወንዶች ልጆችን ወለደ፤ ዚምሪም ሞጻን
ወለደ፤ 43 ሞጻም ቢንዓን ወለደ፤ ቢንዓም ረፋ
ያን ወለደ፤ ረፋያም ኤልዓሳን ወለደ፤ ኤልዓ
ሳም አጺልን ወለደ።
44 አጺልም ዓዝሪቃም፥ ቦክሩ፥ እስማኤል፥
ሸዓርያ፥ ዖባድያና ሐናን ተብለው የሚጠሩትን
ስድስት ወንዶች ልጆችን ወለደ።

## ምዕራፍ 10

### የንጉሥ ሳኦል መሞት
(1 ሳሙ. 31፥1-13)

1 ፍልስጥኤማውያን ወደ ጊልቦዓ ተራራ መጥ
ተው በእስራኤላውያን ላይ አደጋ ጣሉ፤ በዚያም
ጦርነት ብዙ እስራኤላውያን ተገደሉ፤ ከእነርሱ
የተረፉትም ንጉሥ ሳኦልና ወንዶች ልጆቹ
ጭምር ሸሹ፤ 2 ፍልስጥኤማውያን ግን ተከታት
ለው ከሳኦል ልጆች ሦስቱን ዮናታንን፥ አቢናዳብ
ንና ማልኪሹዓን ገደሉ፤ 3 ሳኦል በነበረበት ግን
ባር ጦርነቱ እጅግ ተፋፍሞ ስለነበር ሳኦል በጠ
ላት ፍላጻ ተመትቶ ክፉኛ ቈሰለ፤ 4 እርሱም
በዚህ ጊዜ ወጣት ጋሻ ጃግሬውን “እነዚህ አረማ
ውያን የሆኑ ፍልስጥኤማውያን በማሠቃየት መሳ
ለቂያ እንዳያደርጉኝ ሰይፍህን መዝዘህ ግደለኝ”
አለው፤ ወጣቱ ግን ይህን ለማድረግ እጅግ ፈራ፤
ስለዚህም ሳኦል የራሱን ሰይፍ መዝዞ በመሬት
ላይ በመትከል በላዩ ላይ ወደቀ፤ 5 ወጣቱም የሳኦ
ልን መሞት ባየ ጊዜ እርሱም የገዛ ሰይፉን በመ
ሬት ላይ በመትከል በላዩ ላይ ወድቆ ሞተ። 6 ስለ
ዚህ ሳኦልና ሦስት ወንዶች ልጆቹ በአንድ ላይ
ሞቱ፤ የመንግሥቱም ፍጻሜ ሆነ። 7 በኢይዝራ
ኤል ሸለቆ ይኖሩ የነበሩት እስራኤላውያን ሠራ
ዊቱ እንደሸሸ፥ ሳኦልና ልጆቹም እንደሞቱ
በሰሙ ጊዜ ከተሞቻቸውን ለቀው ሸሹ፤ ፍልስጥ
ኤማውያንም መጥተው ከተሞቻቸውን ያዙ።
8 በጦርነቱ ማግሥት ፍልስጥኤማውያን የሞ
ቱትን እስራኤላውያን ንብረት ለመዝረፍ በሄዱ
ጊዜ የሳኦልና የልጆቹ ሬሳ በጊልቦዓ ተራራ ላይ
ተጋድሞ አገኙ፤ 9 የሳኦልን ራስ ቈርጠው የጦር
መሣሪያውን ከገፈፉ በኋላ በመልእክተኞች አስ
ይዘው የምሥራቹን ለአማልክቶቻቸውና ለሕዝባ
ቸው ይነግሩላቸው ዘንድ ላኩአቸው። 10 የሳኦ
ልን የጦር መሣሪያዎች ከቤተ መቅደሶቻቸው

የሆኑትን ሌዋውያንን ሹሙአቸው” በማለት
የሌዋውያኑን መሪዎች አዘዘ፤ 17-21 ከመዘምራን
ጕሳ የነሐስ ጸናጽል የሚያንሿሹ የዮኤል ልጅ
ሄማን፣ የእርሱ ዘመድ የሆነው የበራክያ ልጅ
አሳፍ፣ እንዲሁም ከመራሪ ጕሳ የቁሳያ ልጅ
ኤታን ተመረጡ፤ በከፍተኛ ድምፅ የሚደረደረ
ውን በገና በመምታት የእነርሱ ረዳቶች እንዲሆ
ኑም ዘካርያስ፣ ያዕዚኤል፣ ሸሚራሞት፣ ይሒ
ኤል፣ ዑኒ፣ ኤሊአብ፣ ማዕሤያና በናያ ተመ
ረጡ።

በዝቅተኛ ድምፅ የሚደረደረውን በገና እንዲ
መቱ ማቲትያ፣ ኤሊፈሌ፣ ሚቅኔያ፣ ዐዛዝያ
እንዲሁም ከቤተ መቅደስ ዘበኞች መካከል ዖቤ
ድኤዶምና ዩዒኤል ተብለው የሚጠሩት ሰዎች
ተመረጡ።

22 ክናንያ የሙዚቃ ችሎታ ስለነበረው ለሌዋ
ውያኑ መዘምራን መሪ ሆኖ ተመረጠ፤
23-24 በራክያ፣ ኤልቃና፣ ዖቤድኤዶምና ዩሒያ
የቃል ኪዳኑ ታቦት ጠባቂዎች ሆነው ተመ
ረጡ፤ ካህናቱ ሸባንያ፣ ዮሻፋጥ፣ ናትናኤል፣
ዐማሳይ፣ ዘካሪያስ፣ በናያና ኤሊዔዘር በቃል
ኪዳኑ ታቦት ፊት ፊት እየሄዱ መለከት እንዲ
ነፉ ተመረጡ።

### የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ
(2 ሳሙ. 6፥12-22)

25 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ዳዊት፣ የእስራኤል
ሕዝብ መሪዎችና የጦር አዛዦዎች የቃል ኪዳ
ኑን ታቦት ለማምጣት ወደ ዖቤድኤዶም ቤት
ሄዱ፤ ከፍ ያለ የደስታ ሥነ ሥርዓትም አደ
ረጉ፤ 26 የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸከሙትን
ሌዋውያን እግዚአብሔር ይረዳቸው ዘንድ ሰባት
ኮርማዎችንና ሰባት በጎችን ሠዉ፤ 27 ዳዊት
ከጥሩ በፍታ የተሠራ መጐናጸፊያና ኤፉድ
ለብሶ ነበር፤ እንዲሁም መዘምራኑ በሙሉ፣
የመዘምራኑ መሪ ክናንያና የቃል ኪዳኑን ታቦት
የተሸከሙት ሌዋውያን ከጥሩ በፍታ የተሠራ
ልብስ ለብሰው ነበር። 28 በዚህ ዐይነት ሁኔታ
መላው የእስራኤል ሕዝብ ጥሩምባና ቀንደ መለ
ከት እየነፉ፣ ጸናጽል እያንሿሹ፣ መሰንቆና
በገና እየደረደሩ በሆታና በእልልታ የቃል ኪዳ
ኑን ታቦት አጅበው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።

29 ታቦቱ ወደ ከተማይቱ በመግባት ላይ ሳለ
የሳኦል ልጅ ሚካል ንጉሥ ዳዊት በደስታ ሲያ
ሸበሽብና ሲዘል በመስኮት ተመለከተች፤ በልብ
ዋም ናቀችው።

## ምዕራፍ 16

1 የቃል ኪዳኑንም ታቦት ወስደው ዳዊት ባዘ
ጋጀው ድንኳን ውስጥ አኖሩት፤ ከዚያም በኋላ
በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንና ለደኅንነት
የሚሆነውን የኅብረት መሥዋዕት ለእግዚአብ
ሔር አቀረቡ፤ 2 ዳዊት መሥዋዕት የማቅረቡን
ሥነሥርዓት ከጨረሰ በኋላ ሕዝቡን በእግዚአብ
ሔር ስም ባረከ፤ 3 ለሕዝቡም ሁሉ ምግብ አከ
ፋፈለ፤ ለወንድም ሆነ ለሴት በእስራኤል ለሚ
ኖር እያንዳንዱ ሰው አንድ ሙልሙል ዳቦ፣
ጥቂት የተጠበሰ ሥጋና ጥቂት ዘቢብ ሰጠ።

4 በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ሆነው
ምስጋና፣ ውዳሴና ክብር በማቅረብ አምላክ
ለሆነው ለእግዚአብሔር የሚደረገውን የአምልኮ
ሥነ ሥርዓት እንዲመሩ ዳዊት ጥቂት ሌዋውያ
ንን ሾመ። 5 አሳፍ መሪ፣ ዘካርያስም የእርሱ
ረዳት ሆነው ተሾሙ፤ ይዒኤል፣ ሸሚራሞት፣
ይሒኤል፣ ማቲትያ፣ ኤሊአብ፣ በናያ፣ ዖቤድ
ኤዶምና ይዒኤል መሰንቆና በገና ለመደርደር፣
አሳፍም ጸናጽል ለማንሿሿት ተመደቡ፤ 6 በና
ያና ያሐዚኤል ተብለው የሚጠሩት ሁለት ካህ
ናት በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ዘወትር
መለከት እንዲነፉ ተመደቡ፤ 7 ዳዊት፣ ለአሳ
ፍና ለቀሩት ሌዋውያን ወገኖቹ ለእግዚአብሔር
የምስጋና መዝሙር የማቅረብ ኀላፊነት የሰጣ
ቸው በዚያን ጊዜ ነበር።

### የምስጋና መዝሙር
(መዝ. 105፥1-15፤ 96፥1-13፤ 106፥1፥47-48)

8 እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ታላቅነቱንም አብሥሩ፤
ያደረገውንም ሁሉ ለሕዝቦች ንገሩ፤
9 ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር
ዘምሩ፤
ያደረገውን አስደናቂ ነገር ሁሉ
ተናገሩ፤
10 በቅዱስ ስሙ ደስ ይበላችሁ፤
እግዚአብሔርን የሚፈልግ ሰው ሁሉ
ሐሴት ያድርግ፤
11 የእርሱን ዕርዳታ ለማግኘት
እግዚአብሔርን ፈልጉ፤
ባለማቋረጥም ለእርሱ ስገዱ፤
12-13 እናንተ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ
የሆነው የያዕቆብ ዝርያዎች፣
እናንተ፣ እግዚአብሔር የመረጠው
የእስራኤል ዝርያዎች፣
እግዚአብሔር ያደረገውን ተአምራትና
የሰጠውን ፍርድ አስታውሱ፤
14 እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤
ትእዛዙም በዓለም ሁሉ ነው፤
15 የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አትርሱ፤
እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለዘላለም
ያጸናል፤
16 ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን
ይጠብቃል፤

16፥16 ፡- ዘፍ. 12፥7፤ 26፥3።

ለዘላለም ‘የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የእስራ
ኤል አምላክ ነው!’ ይላሉ ፤ መንግሥቴንም ለዘ
ላለም ታጸናዋለህ ፤ 25 አምላኬ ሆይ! አገልጋይህ
ለሆንሁት ለእኔ ይህን ሁሉ ስለገለጥኽልኝና ዘሮ
ቼንም እንደምታነግሣቸው ስለነገርኸኝ ይህን
ጸሎት ወደ አንተ ለማቅረብ ድፍረት አግኝቻ
ለሁ ፤ 26 እግዚአብሔር ሆይ! አንተ እውነተኛ
አምላክ ነህ ፤ ይህንንም አስደናቂ የተስፋ ቃል
ለእኔ ሰጥተኸኛል ፤ 27 ባለማቋረጥ በአንተ ፊት
የተወደዱ ይሆኑ ዘንድ ዘሮቼን እንድትባርክ
እለምንሃለሁ ፤ እግዚአብሔር ሆይ! አንተ በእር
ግጥ ሕዝብህን ባርከሃቸዋል ፤ የአንተም በረከት
ለዘላለም በእነርሱ ላይ ይሆናል ።”

## ምዕራፍ 18

### ዳዊት በጦርነት የተቀዳጃቸው ድሎች

(2 ሳሙ. 8፥1-18)

1 ጥቂት ዘግየት ብሎም ንጉሥ ዳዊት እንደ
ገና በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ በመጣል
ድል አደረጋቸው ፤ የጋትን ከተማና በዙሪያዋ
ያሉትን መንደሮች ከእነርሱ ቊጥጥር ነፃ አደ
ረገ ፤ 2 ሞአባውያንንም ድል ነሥቶ እንዲገብሩ
ለት አደረገ ።
3 ቀጥሎም ንጉሥ ዳዊት በሶርያ አገር በሐ
ማት ግዛት አጠገብ በምትገኘው በጾባ ንጉሥ
በሀዳድዔዜር ላይ አደጋ ጣለ ፤ ምክንያቱም ሀዳ
ድዔዜር ከላይ በኩል በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ
ያለውን ግዛት በቊጥጥሩ ሥር ለማድረግ ዘምቶ
ስለነበር ነው ፤ 4 ዳዊት የሀዳድዔዜርን አንድ ሺ
ሠረገላዎች ፥ ሰባት ሺ ፈረሰኞችና ሃያ ሺ እግ
ረኛ ሠራዊት ማረከ ፤ አንድ መቶ ሠረገላ
የሚጐትቱ ፈረሶችን ለራሱ አስቀርቶ የቀሩትን
ፈረሶች በሙሉ እግራቸውን በመቊረጥ ሰነከለ ።
5 በደማስቆ ያሉ ሶርያውያን ንጉሥ ሀዳድዔ
ዜርን ለመርዳት ሠራዊት በላኩ ጊዜ ዳዊት በእ
ነርሱም ላይ አደጋ ጥሎ ሃያ ሁለት ሺ ወታደሮ
ችን ገደለ ፤ 6 ከዚያም በኋላ በግዛታቸው ላይ
የጦር ሰፈር አቋቋመ ፤ ሕዝቡም ግብር እየከ
ፈሉ ሰጥ ለጥ ብለው ለእርሱ ተገዙ ፤ እግዚአብ
ሔር ዳዊትን በየሰፍራው ድል አድራጊ አደረ
ገው ፤ 7 ዳዊት የሀዳድዔዜር ባለሟሎች የሆኑ
ባለሥልጣኖች አንግበውት የነበረውን ከወርቅ
የተሠራ ጋሻ ሁሉ ማርኮ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰ
ደው ፤ 8 እንዲሁም የሀዳድዔዜር ግዛት ከነበሩት
ከጢብሐትና ከኩን ከተማዎች እጅግ ብዙ የሆነ
ነሐስ ወሰደ ፤ ዘግየት ብሎም ሰሎሞን በነሐሱ
የቤተ መቅደሱን በርሜል ፥ ዐምዶችና የነሐስ
ዕቃዎች አሠራበት ።
9 የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት የሀዳድዔዜርን
መላ ሠራዊት ድል አድርጎ እንደ ደመሰሰ
ሰማ ፤ 10 ቶዑ ከሀዳድዔዜር ጋር ብዙ ጊዜ ጦር
ነት አድርጎ ስለነበር ፥ ንጉሥ ዳዊትን እጅ እን
ዲነሣና በሀዳድዔዜር ላይ ስለተቀዳጀው ድል
ደስታውን እንዲገልጥለት ልጁን ዮራምን ወደ
ዳዊት ላከ ። ዮራምም ከወርቅ ፥ ከብርና ከነሐስ
የተሠሩ ዕቃዎችን ገጸ በረከት አድርጎ ለዳዊት
አመጣለት ፤ 11 ንጉሥ ዳዊትም እነርሱን ወስዶ
ከኤዶም ፥ ከሞአብ ፥ ከዐሞን ፥ ከፍልስጥኤምና
ከዐማሌቅ ማርኮ ካመጣቸው ከወርቅ ፥ ከብርና
ከነሐስ ከተሠሩ ዕቃዎች ጋር ለአምልኮ ሥነ ሥ
ርዓት መገልገያ እንዲሆኑ አደረጋቸው ።
12 የጸሩያ ልጅ አቢሻይ ኤዶማውያንን
በጨው ሸለቆ ውስጥ ድል አድርጎ ከእነርሱ
መካከል ዐሥራ ስምንት ሺ የሚሆኑትን ገደለ ፤
13 በመላው የኤዶም ግዛት ውስጥ የጦር ሰፈሮ
ችን አቋቋመ ፤ በዚያም የሚኖሩ ሕዝብ የን
ጉሥ ዳዊት ገባሮች ሆኑ ፤ እግዚአብሔር ዳዊ
ትን በሁሉ ሰፍራ ድል አድራጊ አደረገው ።
14 ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ ፤
ሕዝቡም ሁል ጊዜ አድልዎ የሌለበት ፍትሕ
እንዲያገኙ አደረገ ። 15 የአቢሻይ ወንድም ኢዮ
አብ የሠራዊቱ አዛዥ ነበር ፤ የአሒሉድ ልጅ
ይሆሻፋጥ የቤተ መዛግብት ኀላፊ ነበር ፤ 16 የአ
ሒጡብ ልጅ ሳዶቅና የአብያታር ልጅ አቢሜ
ሌክ ካህናት ነበሩ ፤ ሠራያ የቤተ መንግሥት
ጸሐፊ ነበር ፤ 17 የዮዳሄ ልጅ በናያ የዳዊት
ክብር ዘብ አዛዥ ነበር ፤ የንጉሥ ዳዊት ወን
ዶች ልጆች በአባታቸው መንግሥት ከፍተኛ
ማዕርግ ነበራቸው ።

## ምዕራፍ 19

### ዳዊት ዐሞናውያንንና ሶርያውያንን ድል አደረገ

(2 ሳሙ. 10፥1-19)

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዐሞን ንጉሥ ናዖስ
ሞተ ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ ልጁ ሐኑን
ነገሠ ፤ 2 ንጉሥ ዳዊትም “አባቱ ናዖስ ለእኔ
እንዳደረገልኝ ሁሉ ፥ እኔም ለልጁ ለሐኑን
ታማኝ ወዳጅ በመሆን ወሮታውን እከፍላለሁ”
አለ ፤ ስለዚህም ዳዊት የሐዘን ተካፋይነቱን
ለመግለጥ መልእክተኞች ላከ ።
መልእክተኞቹም ወደ ዐሞን ምድር በደረሱ
ጊዜ ፥ 3 ዐሞናውያን ባለሥልጣኖች ንጉሡን እን
ዲህ አሉት ፥ “ዳዊት እነዚህን ሰዎች የላከው
አባትህን በማክበር የሐዘንህ ተካፋይ ለመሆን
ይመስልሃልን? ከቶ እንዳይመስልህ ፤ እርሱ እነ
ዚህን መልእክተኞች የላከው ምድሪቱን ወርሮ
መያዝ ይችል ዘንድ እንዲሰልሉለት ነው ።”
4 ስለዚህ ሐኑን የዳዊትን መልእክተኞች ይዞ
ጢማቸውን ላጨ ፤ ሐፍረተ ሥጋቸው እስኪ
ታይ ድረስ ከወገባቸው በታች ያለውን ልብስ
ቈረጠና ወደ አገራቸው ሰደዳቸው ፤ 5 እነርሱም

18፥8 ፦ 1ነገ. 7፥40-47 ፤ 2ዜ.መ. 4፥11-18 ። 18፥12 ፦ መዝ. 60 ።

የወይራ ዘይት ግምጃ ቤት አስተዳዳሪ ፦
  ኢዮአስ
በሳሮን ሜዳ የሚገኙት የቀንድ ከብቶች
  አስተዳዳሪ ፦ የሳሮን ተወላጅ
  የሆነው ሺጥራይ
በሸለቆዎች የሚገኙ የቀንድ ከብቶች
  አስተዳዳሪ ፦ የዓድላይ ልጅ ሻፋጥ
የግመሎች አስተዳዳሪ ፦ እስማኤላዊው
  ኦቢል
የአህዮች አስተዳዳሪ ፦ የሜሮኖት
  ተወላጅ የሆነው ዬሕድያ
የበጎችና የፍየሎች አስተዳዳሪ ፦
  ሀግራዊው ያዚዝ

### የዳዊት የግል አማካሪዎች

32 የንጉሥ ዳዊት አጐት የሆነው ዮናታን
ብልህ አማካሪና የታወቀ ምሁር ነበር ፤ እርሱና
የሐክሞኒ ልጅ ይሒኤል የንጉሡ ልጆች አስተ
ማሪዎች ነበሩ ፤ 33 አኪጦፌል የንጉሡ አማካሪ
ሲሆን ፥ አርካዊው ሑሻይ የንጉሡ ወዳጅና
የግል አማካሪ ነበር ፤ 34 አኪጦፌል ከሞተ በኋ
ላም አብያታርና የበናያ ልጅ ዮሆያዳዕ የንጉሡ
አማካሪዎች ሆኑ ፤ ኢዮአብ ደግሞ የንጉሡ
ሠራዊት አዛዥ ነበር ።

## ምዕራፍ 28

### ዳዊት ስለ ቤተ መቅደሱ ሥራ የሰጠው መመሪያ

1 ንጉሥ ዳዊት የእስራኤል ባለ ሥልጣኖች
በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው እንዲሰበሰቡ
ትእዛዝ አስተላለፈ ፤ ስለዚህ የየነገዱ መሪዎች ፥
የመንግሥቱን ሥራ የሚያካሂዱ ባለሥልጣ
ኖች ፥ የጦሳ አለቆች ፥ የንጉሡንና የወንዶች
ልጆቹን ንብረትና የቀንድ ከብት ተቈጣጣሪዎች
እንዲሁም የቤተ መንግሥት ባለሟሎች ፥ ዝነ
ኞች የሆኑ ጦረኞችና ታዋቂ የሆኑ ሰዎች
በሙሉ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ ።
2 ዳዊትም በፊታቸው ቆሞ እንዲህ አላ
ቸው ፥ "የአገሬ ሰዎች ሆይ! አስቲ አድም
ጡኝ ፤ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የእግሩ
መረገጫ የሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት ለዘለቄ
ታው የሚኖርበትን ቤት ለመሥራት በመፈለግ
ዝግጅት አድርጌ ነበር ፤ 3 ነገር ግን እኔ ወታደር
በመሆኔና ብዙ ደምም በማፍሰሴ ቤተ መቅደስ
እንድሠራለት እግዚአብሔር አልፈቀደልኝም ፤
4 የእስራኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ፥ እስ
ራኤልን ለዘላለም እናስተዳድር ዘንድ እኔንና
ዘርያዎቼን መርጦአል ፤ የሕዝብ መሪዎችን ያስ
ገኝ ዘንድ የይሁዳን ነገድ መርጦአል ፤ ከይሁ
ዳም ነገድ የአባቴን ቤተሰብ መርጦአል ፤ በዚ
ያም ቤተሰብ ካሉት ሁሉ እኔን መርጦ በመ
ላው እስራኤል ላይ ያነግሠኝ ዘንድ በጎ ፈቃዱ
ሆኖአል ። 5 ለእኔም ብዙ ወንዶች ልጆችን
ሰጠኝ ፤ ከእነርሱም ሁሉ መካከል የእግዚአብ
ሔር መንግሥት በሆነው በመላው እስራኤል
ላይ ይነግሥ ዘንድ ሰሎሞንን መርጦታል ።
6 "እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛል ፥ 'ለእኔ
ቤተ መቅደስ የሚሠራልኝ ልጅህ ሰሎሞን
ነው ፤ እኔ እርሱን ልጄ እንዲሆን መርጬዋ
ለሁ ፤ እኔም ለእርሱ አባት እሆነዋለሁ ፤ 7 እርሱ
አሁን በሚያደርገው ዐይነት ዘወትር ሕጌንና
ትእዛዜን በጥንቃቄ የሚፈጽም ከሆነ ፥ መንግሥ
ቱን ለዘላለም አጸናለታለሁ ።'
8 "አሁንም ሕዝቤ ሆይ! በእግዚአብሔርና
የእግዚአብሔር ሕዝብ በሆነው በዚህ በመላው
የእስራኤል ጉባኤ ፊት አምላካችን እግዚአብ
ሔር ያዘዘንን ሁሉ በጥንቃቄ ትፈጽሙ ዘንድ
ዐደራ እላችኋለሁ ፤ ይህን ብታደርጉ ይህችን
መልካም ምድር ለዘለቄታው ርስታችሁ ታደር
ጋላችሁ ፤ ወደፊት ለሚመጡትም ትውልዶች
ማስተላለፍ ትችላላችሁ ።"
9 ዳዊት ሰሎሞንንም እንዲህ አለው ፥ "ልጄ
ሆይ! የአባትህን አምላክ እንድታውቅ ፥ በሙሉ
ልብና በፈቃደኛ አእምሮ እንድታገለግለው
ዐደራ እልሃለሁ ፤ እርሱ አሳባችንንና ምኞታች
ንን ሁሉ ያውቃል ፤ ወደ እርሱ ብትቀርብ እር
ሱም ወደ አንተ ይቀርባል ፤ ብትተወው ግን
እርሱም ለዘላለም ይተውሃል ፤ 10 ቅዱስ ቤተ
መቅደሱን ትሠራለት ዘንድ እግዚአብሔር አን
ተን እንደመረጠህ አትዘንጋ ፤ አሁንም በርትተህ
በቈራጥነት ሥራው ።"
11 ዳዊት ለሰሎሞን የቤተ መቅደሱን ሕንጻ
ዎች ሁሉ የዕቃ ግምጃ ቤቶቹንና የሌሎቹንም
ክፍሎች ሁሉ እንዲሁም ኃጢአት የሚሰረይበ
ትን የቅድስተ ቅዱሳኑን አሠራር የሚገልጥ
ዕቅድ ሰጠው ። 12 ለአደባባዮቹና በዙሪያቸው
ላሉት ክፍሎች ፥ ለቤተ መቅደሱ ዕቃና ለእግዚ
አብሔር ለቀረቡ መባዎች የዕቃ ግምጃ ቤት
ሁሉ በአእምሮው የያዘውን የአሠራር ዕቅድ
ጨምሮ ሰጠው ። 13 እንዲሁም ዳዊት ካህናቱና
ሌዋውያኑ ተግባራቸውን የሚያከናውኑበትን ፥
የቤተ መቅደሱን ሥራ የሚያካሄዱበትንና
የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች ሁሉ የሚከባከቡበ
ትን አደረጃጀት የሚያሳየውን ዕቅድ ሰጠው ።
14 ከዚህ በታች ለተመለከቱት ዕቃዎች ማሠሪያ
ምን ያህል ብርና ወርቅ እንደሚያስፈልግ መመ
ሪያ ሰጠ ፤ ለልዩ ልዩ ዕቃዎች ፥ 15 ለእያንዳንዱ
ቀንዲልና ለእያንዳንዱ መቅረዝ ፥ 16 ከብር ለሚ
ሠሩት ጠረጴዛዎች ፥ ለእግዚአብሔር መባ ሆኖ
የሚቀርበው ኅብስት ለሚቀመጥበት ከወርቅ
ለሚሠራው ለእያንዳንዱ ገበታ ፤ 17 እንዲሁም

28፥2-7 ፦ 2ሳሙ. 7፥1-6 ፤ 1ዜ.መ. 17፥1-14 ።

የምናመልክበት፥ የተቀደሰውን ኅብስት ሳናቋ
ርጥ ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት፥ በየቀኑ
ጠዋትና ማታ፥ እንዲሁም በሰንበታት፥ በወር
መባቻዎችና በሌሎችም በተቀደሱ በዓላት እግ
ዚአብሔር አምላካችንን ለማክበር የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕት የምናቀርብበት የተቀደሰ ስፍራ
ይሆናል፤ የእስራኤል ሕዝብ ይህን ለዘላለም
እንዲያደርጉ እግዚአብሔር አዝዞአል። 5 የእኛ
አምላክ ከሌሎች አማልክት ሁሉ ይበልጥ
ታላቅ ስለሆነ፥ ታላቅ፥ ቤተ መቅደስ ልሠራ
ለት ዐቅጃለሁ። 6 እንደ እውነቱ ከሆነ ለእግዚአ
ብሔር በቂ የሚሆን ቤተ መቅደስን ለመሥራት
የሚችል ማንም የለም፤ ምክንያቱም የሰማይና
የምድር ስፋት እንኳ እግዚአብሔርን ሊይዘው
አይችልም፤ ታዲያ ለእግዚአብሔር ዕጣን ለማ
ጠን የሚበቃ ቤት ከመሥራት በቀር ለእርሱ
ማደሪያ ሊሆን የሚችል ቤተ መቅደስ ለመሥ
ራት የምሞክር እኔ ማን ነኝ? 7 እንግዲህ ቅር
ጽን የማውጣት፥ ወርቅን፥ ብርን፥ ነሐስንና
ብረትን የማቅለጥ፥ ሰማያዊ፥ ሐምራዊና ቀይ
ልብስ የመሥራት ችሎታ ያለውን ብልኀተኛ
ሰው ላክልኝ፤ እርሱም አባቴ ዳዊት ከመረጣ
ቸው በይሁዳና በኢየሩሳሌም ካሉት ብልኀተ
ኞች ሰዎች ጋር ይሠራል። 8 የአንተ እንጨት
ቈራጮች እጅግ የሠለጠኑ መሆናቸውን ዐውቃ
ለሁ፤ ስለዚህ ከሊባኖስ የዝግባ፥ የጥድና የሰን
ደል እንጨት ላክልኝ፤ እኔም ብዙ እንጨት
ቈርጠው በማዘጋጀት የአንተን ሰዎች የሚረዱ፥
9 የእኔን ሰዎች ወደ አንተ ለመላክ ዝግጁ ነኝ፤
ምክንያቱም ይህ እኔ ልሠራው ያቀድሁት ቤተ
መቅደስ ሰፊና እጅግ የተዋበ መሆን ይገባዋል፤
10 ለሠራተኞችህ ስንቅ የሚሆን ሁለት ሚሊዮን
ኪሎ ስንዴ፥ ሁለት ሚሊዮን ኪሎ ገብስ፥
አራት መቶ ሺ ሊትር የወይን ጠጅና አራት
መቶ ሺ ሊትር የወይራ ዘይት እልክልሃለሁ።”

11 ንጉሥ ኪራምም ለንጉሥ ሰሎሞን በደብ
ዳቤ እንዲህ ሲል መለሰለት፥ “እግዚአብሔር
ሕዝቡን ስለሚወድ አንተ በእነርሱ ላይ እንድት
ነግሥ አደረገ። 12 ሰማይንና ምድርን የፈጠረ፥
በጥበብ፥ በማስተዋልና በብልኀት የተሞላ
ልጅን ለንጉሥ ዳዊት የሰጠ፥ የእስራኤል አም
ላክ የሆነ እግዚአብሔር ይመስገን! ይህም ልጅ
ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፥ ለራሱም ቤተ
መንግሥት ለመሥራት ዐቅዶአል። 13 እነሆ ጥበ
በኛና በእጅ ሥራ የሠለጠነ ሑራም ተብሎ
የሚጠራ ብልኀተኛ ሰው ልኬልሃለሁ። 14 የሑ
ራም እናት ከዳን ነገድ ስትሆን፥ አባቱም የጢ
ሮስ ተወላጅ ነው፤ ሑራም ከወርቅ፥ ከብር፥
ከነሐስ፥ ከብረት፥ ከድንጋይና ከእንጨት ልዩ
ልዩ ነገሮችን የመሥራት ችሎታ አለው፤ እንዲ
ሁም ከሰማያዊ፥ ከሐምራዊ፥ ከቀይ ጨርቅና
ከበፍታ የተለያየ ልብስ መሥራት ይችላል፤
ከዚህም ሌላ ልዩ ልዩ ቅርጽ ማውጣትና በተሰ
ጠውም ንድፍ መሠረት ሁሉን ነገር መሥራት
ይችላል፤ ስለዚህ ይህን ሰው በእጅ ሥራ ከሠለ
ጠኑ ከአንተ ሰዎችና ከእነዚያ ለአባትህ ይሠሩ
ከነበሩ ሰዎች ጋር እንዲሠራ አድርገው። 15 እን
ግዲህ ልትልክልን በሰጠኸን ቃል መሠረት ስን
ዴውን፥ ገብሱን፥ የወይን ጠጁንና የወይራ ዘይ
ቱን ላክልን፤ 16 እኛም የምትፈልገውን የዝግባ
እንጨት ሁሉ ከሊባኖስ ተራራዎች ቈርጠን
አንድነት በማሰር በባሕር ላይ ተንሳፍፎ እስከ
ኢዮጴ እንዲደርስ እናደርጋለን፤ ከዚያም ወደ
ኢየሩሳሌም ልትወስደው ትችላለህ።”

### የቤተ መቅደሱ ሥራ አጀማመር
(1 ነገ. 6፥1-38)

17 ንጉሥ ሰሎሞን ከዚህ በፊት አባቱ ዳዊት
ባደረገው ዐይነት በእስራኤል ምድር የሚኖሩ
ትን የውጭ አገር ሰዎች ቈጠረ፤ በዚህም ዐይ
ነት በግዛቱ ውስጥ አንድ መቶ ኀምሳ ሦስት ሺ
ስድስት መቶ የውጭ አገር ሰዎች መኖራቸው
ተረጋገጠ፤ 18 ከእነርሱም መካከል ሰባው ሺ
ዕቃ እንዲያጓጉዙ፥ ሰማኒያው ሺ በተራራዎች
ላይ ድንጋይ እንዲፈልጡ አደረገ፤ ደግሞም
ሥራው በትክክል መካሄዱን የሚቈጣጠሩ
ሦስት ሺ ስድስት መቶ ሰዎችን ሾመ።

## ምዕራፍ 3

1 የሰሎሞን አባት ንጉሥ ዳዊት ቤተ መቅ
ደስ የሚሠራበትን ስፍራ በኢየሩሳሌም በሞሪያ
ተራራ ላይ አስቀድሞ አዘጋጅቶ ነበር፤ ይህም
ስፍራ እግዚአብሔር ለንጉሥ ዳዊት የተገለጠ
ለት፥ ኢያቡሳዊው ኦርና አውድማ አድርጎ
ይጠቀምበት የነበረ ነው። 2 ሰሎሞን በነገሠ በአ
ራተኛው ዓመት፥ ዘሁለተኛው ወር የቤተ
መቅደሱን ሥራ ጀመረ፤ 3 ንጉሥ ሰሎሞን ያሠ
ራው ቤተ መቅደስ ርዝመቱ ሃያ ሰባት ሜትር
ሲሆን፥ ወርዱ ዘጠኝ ሜትር ነበር፤ 4 በመግቢ
ያው በር ያለው በረንዳም ቁመቱ ኀምሳ አራት
ሜትር ሲሆን፥ ወርዱ ልክ እንደ ቤተ መቅደሱ
ወርድ ዘጠኝ ሜትር ነው፤ ውስጡም በንጹሕ
ወርቅ ተለብጦ ነበር። 5 የቤተ መቅደሱ ዋና
ክፍል በጥድ እንጨትና በንጹሕ ወርቅ የተለ
በጠ ሆኖ የዘንባባና የሰንሰለት ቅርጽ ተሰሎበት
ነበር። 6 ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እጅግ
ውብ በሆነ የከበረ ድንጋይና ከፋርዋይም አገር
በመጣ ወርቅ አስጊጦት ነበር። 7 የቤተ መቅደ
ሱን ግንቦች፥ የጣራውን ክፈፎች፥ መቃኖችና
መዝጊያዎቹን በወርቅ ለበጣቸው፤ በግንቦቹም
ላይ የኪሩቤልን ምስሎች ቀረጸባቸው። 8 ቅድ
ስቷ ቅዱሳን ተብሎ የሚጠራው የውስጠኛው

2፥6 ፦ 1ነገ. 8፥27፤ 2ዜ.መ. 6፥18። 3፥1 ፦ ዘፍ. 22፥2። 3፥8 ፦ ዘጸ. 26፥33-34።

ሁለት ምሰሶዎች፥
በምሰሶዎቹ ጫፍ ላይ የሚገኙት የሳሕን
ቅርጽ ያላቸው ሁለት ጉልላቶች፥
በእያንዳንዱ ጉልላት ላይ የሚገኙት
በመርበብ አምሳል የተቀረጹት
ሰንሰለቶች፥
በእያንዳንዱ ጉልላት ላይ በሁለት ዙር
የተቀረጹ ከነሐስ የተሠሩ አራት
መቶ የሮማን ፍሬ ምስሎች፥
ዐሥሩ ባለመንኰራኲር የዕቃ
ማስቀመጫዎች፥
ዐሥሩ የመታጠቢያ ገንዳዎች፥
ትልቁ በርሜል፥
በርሜሉን ደግፈው የያዙት የዐሥራ
ሁለቱ ኮርማዎች ቅርጾች፥
ምንቸቶች፥ መጫሪያዎች፥ ሜንጦዎችና
ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ
ዕቃዎች በእጅ ጥበብ ሥራ።
ታዋቂ የሆነው ሑራም በንጉሥ ሰሎሞን ትእ
ዛዝ መሠረት ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገ
ልግሎት ይውሉ ዘንድ እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ
የሠራው ከተወለወለ ነሐስ ነበር።
17 ንጉሥ ሰሎሞን እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ
ያሠራው በዮርዳኖስ ሸለቆ፥ በሱኮትና በጸሬዳ
መካከል በሚገኘው በነሐስ ማቅለጫ ስፍራ
ነበር፤ 18 በዚህ ዐይነት የተሠሩት ዕቃዎች
እጅግ ብዙ ስለነበሩ እነርሱን ለማሠራት የተጠ
ቀመበት ጠቅላላ የነሐስ ክብደት ምን ያህል
እንደሆነ ማንም ሊያውቅ አልቻለም።
19 እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞን ለቤተ መቅደሱ
አገልግሎት የሚውሉ የሚከተሉትን ዕቃዎች
ከወርቅ አሠርቶአል፦ መሠዊያውና ለእግዚአብ
ሔር መባ ሆኖ የሚቀርበው ኅብስት ማኖሪያ
ጠረጴዛ፥ 20 ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ መቅረዞችና
በተወሰነው ዕቅድ መሠረት በቤተ መቅደሱ ፊት
ለፊት የሚያበሩ ቀንዲሎቻቸው፥ 21 የአበባ
ቅርጽ ያላቸው ጌጦች፥ ቀንዲሎችና መኰስተሪያ
ዎች፥ 22 የመብራት ማጥፊያዎች፥ ማንቆርቆሪያ
ዎች፥ ጥናዎችና የእሳት መጫሪያዎች፤ እነዚህ
ዕቃዎች ሁሉ ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ ናቸው፤
የቤተ መቅደሱ የውጪ በሮችና የቅድስተ ቅዱ
ሳን በሮችም በወርቅ የተለበጡ ነበሩ።

## ምዕራፍ 5

1 ንጉሥ ሰሎሞን የቤተ መቅደሱን ሥራ
ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ ዳዊት ለእግዚአብሔር
የተለዩ ያደረጋቸውን ብርና ወርቅ እንዲሁም
ሌሎችን ዕቃዎች ሁሉ በቤተ መቅደሱ ውስጥ
በሚገኘው የዕቃ ግምጃ ቤት አኖራቸው።

### የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ
(1 ነገ. 8፥1-9)

2 ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔ
ርን ቃል ኪዳን ታቦት የዳዊት ከተማ ከሆነችው
ከጽዮን ወደ ቤተ መቅደሱ ያመጡ ዘንድ የእስራ
ኤል ሽማግሌዎች፥ የነገድና የቤተሰብ አለቆች
ሁሉ በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ ሰጠ፤
3 በሰባተኛው ወር በሚከበረው በዳስ በዓል ጊዜ
ሁሉም መጥተው በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ፤
4 መሪዎቹ ሁሉ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ ሌዋ
ውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው፥ 5 ወደ
ቤተ መቅደሱ አመጡት፤ እንዲሁም ካህናቱና
ሌዋውያኑ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ድንኳ
ንና በውስጡ የነበሩትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ
ወደ ቤተ መቅደሱ አመጡ። 6 ንጉሥ ሰሎሞንና
ሕዝቡ ሁሉ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ተሰበ
ሰቡ፤ ከዚህም በኋላ ከብዛታቸው የተነሣ ሊቈ
ጠሩ የማይችሉ እጅግ ብዙ በጎችንና የቀንድ ከብ
ቶችን መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ፤ 7 ካህና
ቱም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ወደ
ቤተ መቅደሱ አግብተው በቅድስተ ቅዱሳኑ
ውስጥ ከኪሩቤል ክንፎች በታች በሚገኘው
ስፍራ አኖሩት። 8 የተዘረጉት የኪሩቤል ክንፎች
የቃል ኪዳኑን ታቦትና የታቦቱን መሎጊያዎች
ሸፍነዋቸው ነበር። 9 መሎጊያዎቹ እጅግ ረዣዥ
ሞች ስለነበሩ በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
የቆመ ማንኛውም ሰው ሊያያቸው ይችላል፤
በሌላ አቅጣጫ የቆመ ግን ፈጽሞ ሊያያቸው አይ
ችልም ነበር፤ እነዚህ መሎጊያዎች እስከ ዛሬ
ድረስ በዚያው ይገኛሉ፤ 10 የእስራኤል ሕዝብ
ከግብጽ እንደወጡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር
ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ ሙሴ በሲና ተራራ በቃል
ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ካስቀመጣቸው ከሁለቱ ጽላ
ቶች በቀር በታቦቱ ውስጥ ሌላ ነገር አልነበረም።

### የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ

11-14 እዚያ የነበሩት ካህናት ሁሉ የአገልግ
ሎት ምድባቸውን ሳይመለከቱ በአንድነት ራሳ
ቸውን ለእግዚአብሔር ለጥተው ነበር፤ መዘም
ራን የሆኑ ሌዋውያን ሁሉ፥ አሳፍ፥ ሄማንና
ይዱቱን እንዲሁም ወንዶች ልጆቻቸውና ዘመ
ዶቻቸው ሁሉ ጥሩ የበፍታ ልብስ ለብሰው
ነበር፤ ሌዋውያኑ ጸናጽልና መሰንቆ በመያዝ
በስተ ምሥራቅ በኩል ከመሠዊያው አጠገብ
ቆመው ነበር፤ ከእነርሱም ጋር መለከት የሚ
ነፉ አንድ መቶ ሃያ ካህናት ነበሩ፤ እነዚህ መዘ
ምራን ሁሉ በመለከት፥ በጸናጽል፥ በበገናና
በሌሎችም የሙዚቃ መሣሪያዎች እየታጀቡ፦

5፥1 ፦ 2ሳሙ. 8፥11፤ 1ዜ.መ. 18፥11። 5፥2 ፦ 2ሳሙ. 6፥12-15፤ 1ዜ.መ. 15፥25-28። 5፥10 ፦ ዘዳ. 10፥5።
5፥13 ፦ 1ዜ.መ. 16፥34፤ 2ዜ.መ. 7፥3፤ ዕዝ. 3፥11፤ መዝ. 100፥5፤ 106፥1፤ 107፥1፤ 118፥1፤ 136፥1፤ ኤር. 33፥11።
5፥13-14 ፦ ዘጸ. 40፥34-35።

## ምዕራፍ 8

### ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች

(1 ነገ. 9፥10-28)

1 ሰሎሞን ቤተ መቅደሱንና ቤተ መንግሥ
ቱን ለመሥራት ሃያ ዓመት ፈጀበት ፤ 2 እንዲ
ሁም ንጉሥ ኪራም የሰጠውን ከተማዎች እንደ
ገና ሠርቶ እስራኤላውያን እንዲሰፍሩባቸው
አደረገ ፤ 3 ሰሎሞን በሐማትና በጾባ ግዛቶች ላይ
ዘምቶ በቍጥጥሩ ሥር አደረጋቸው ፤ 4 በበረሓ
የምትገኘውንም የታድሞር ከተማ መሸገ ፤ በሐ
ማት የስንቅና የትጥቅ ማኖሪያ የነበሩትን ከተማ
ዎች ሁሉ እንደገና ሠራ ፤ 5 እንዲሁም ሰሎሞን
የሚከተሉትን ከተማዎች እንደገና ሠራ ፤ እነር
ሱም በላይኛውና በታችኛው ቤትሖሮን በብረት
መዝጊያ ሊዘጉ የሚችሉ ቅጽር በሮች ያሉአ
ቸው የተመሸጉ ከተማዎች ፤ 6 የባዕላት ከተማ ፤
ስንቅና ትጥቅ የሚያስቀምጥባቸው ከተማዎች
ሁሉ ፤ ፈረሶችና ሠረገላዎች የሚኖሩባቸው ከተ
ማዎች ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ ሰሎሞን በኢየ
ሩሳሌም ፥ በሊባኖስና በእርሱ አስተዳደር ባለው
ግዛት በሙሉ ሊያከናውነው ያቀደውን ሁሉ
ፈጸመ ። 7-8 ሰሎሞን በጕልበት ሥራ ያሰማራ
ቸው ገባሮች ፥ እስራኤላውያን ምድራቸውን
ርስት አድርገው በያዙ ጊዜ ያልገደሉአቸው የከ
ነዓን ሕዝብ ዝርያዎች ነበሩ ፤ እነዚህም የከነ
ዓን ዝርያዎች እስከ አሁን ድረስ ባሪያዎች
ሆነው የሚያገለግሉ ሒታውያን ፥ አሞራው
ያን ፥ ፈሪዛውያን ፥ ሒዋውያንና ኢያቡሳውያን
ናቸው ፤ 9 ሰሎሞን ከእስራኤላውያን ወገን ማን
ንም ባሪያ አድርጎ አላሠራም ፤ እስራኤላውያን
ወታደሮች ፥ የጦር መኰንኖች ፥ የጦር አዛዥ
ዎች ፥ ሠረገላ ለሚነዱ ሁሉ ኀላፊዎችና ፈረሰ
ኞች ሆነው ያገለግሉ ነበር ። 10 ሰሎሞን ለሚያ
ከናውነው ልዩ ልዩ የሕንጻ ሥራ ፥ የጕልበት
ሥራ ይሠሩ በነበሩ ለተመደቡት ገባሮች ሁለት
መቶ ኀምሳ ኀላፊዎች ነበሩአቸው ።

11 ሰሎሞን “የእግዚአብሔር ታቦት ያለበት ስፍራ ሁሉ ቅዱስ ስለሆነ ፥ ግብ
ጻዊት ሚስቴ በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት ቤተ
መንግሥት ውስጥ መኖር አይገባትም” በማለት
የግብጽ ንጉሥ ልጅ የሆነችውን ሚስቱን ከዳ
ዊት ከተማ አውጥቶ እርሱ ወዳሠራላት ወደ
ሌላ መኖሪያ ቤት ተዘዋውራ እንድትኖር አደ
ረገ ።

12 ሰሎሞን በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ባሠ
ራው መሠዊያ ላይ ልዩ ልዩ መሥዋዕት ለእግዚ
አብሔር አቀረበ ፤ 13 የሙሴ ሕግ በሚያዝዘው
መሠረትም በእያንዳንዱ የበዓል ቀን ማለትም
በየሰንበቱ ፥ በየወሩ መባቻ ፥ በየዓመቱ በሚከ
በሩ ሦስት በዓላት ማለትም በቂጣ በዓል ፥ በመ
ከር በዓልና በዳስ በዓል የሚቃጠለውን መሥዋ
ዕት ለእግዚአብሔር ያቀርብ ነበር ። 14 አባቱ
ዳዊት የደነገጋቸውን መመሪያዎች በመከተልም
የካህናቱንና ካህናቱን በሥራና መዝሙር በመዘ
መር የሚረዱትን ሌዋውያን የየዕለቱን የሥራ
መደብ አቀናበረ ፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር
ሰው በሆነው በዳዊት ትእዛዝ መሠረት የቤተ
መቅደሱ ዘበኞች በእያንዳንዱ ቅጽር በር የዕለት
ሥራቸውን እንዲያከናውኑ አከፋፍሎ መደበ ።
15 በዚህ ዐይነት ስለ ግምጃ ቤቶችና ስለ ሌሎ
ችም ጒዳዮች ዳዊት ለካህናትና ለሌዋውያን በሰ
ጠው መመሪያ መሠረት አንድም ሳይቀር
ሁሉም በሚገባ ይከናወን ነበር ።

16 በዚህም ጊዜ የሰሎሞን የሥራ ዕቅድ
ሁሉ ፥ ማለትም ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
መሠረት መጣል ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ
ሥራው ሁሉ በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ ።

17 ከዚህ በኋላ ሰሎሞን በኤዶም ምድር በአ
ካባ የባሕር ወሽመጥ ወደብ ወደሆኑት ወደ ዔጽ
ዮንጋብርና ወደ ኤላት ሄደ ፤ 18 ንጉሥ ኪራም
በሠለጠኑ መርከበኞች የሚነዱና በራሱ መኰን
ኖች የሚመሩ መርከቦችን ለሰሎሞን ልኮለት
ነበር ፤ እነርሱም ከሰሎሞን መኰንኖች ጋር
በመሆን ወደ ኦፊር ምድር መጡ ፤ ከዚያም ከዐ
ሥራ አምስት ሺ ኪሎ የሚበልጥ ወርቅ ለሰሎ
ሞን ይዘውለት መጡ ።

## ምዕራፍ 9

### የንግሥተ ሳባ ጒብኝት በኢየሩሳሌም

(1 ነገ. 10፥1-13)

1 ንግሥተ ሳባ ስለ ሰሎሞን የሚነገረውን አስ
ደናቂ ጥበብ ሁሉ ሰማች ፤ ስለዚህ አስቸጋሪ
በሆኑ የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ልትፈትነው ወደ
ኢየሩሳሌም መጣች ፤ ወደ ኢየሩሳሌም ስትመ
ጣም ብዙ የክብር አጀቢዎችን አስከትላ ሽቶ ፥
የከበሩ ዕንቊዎችና እጅግ የበዛ ወርቅ በግመ
ሎች አስጭና ነበር ፤ ከሰሎሞንም ጋር በተገና
ኙች ጊዜ በልብዋ ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበች
ለት ፤ 2 እርሱም ላቀረበችለት ጥያቄ ሁሉ መልስ
ሰጠ ፤ ሊተረጒምላት የተሳነውና ከእርሱ የተሰ
ወረ ምንም ዐይነት እንቆቅልሽ አልነበረም ።
3 ንግሥተ ሳባም ጥበብ የተሞላበትን የሰሎሞንን
አነጋገር አዳመጠች ፤ እርሱ ያሠራውንም ቤተ
መንግሥት አየች ፤ 4 በሰሎሞን ገበታ ላይ የሚቀ
ርበውን የምግብ ዐይነት ፥ የመኳንንቱ የመኖሪያ
አካባቢዎች ፥ የቤተ መንግሥቱን ሠራተኞች
የሥራ አደረጃጀት ፥ የደንብ ልብሳቸውንም ዐይ
ነት ፤ በግብዣ ጊዜ የሚያገለግሉትን አሳላፊዎ
ችና በቤተ መቅደስም የሚያቀርባቸውን መሥዋ
ዕቶችን ሁሉ ተመለከተች ፤ በዚህም ሁሉ የተሰ
ማት አድናቆት ከጠበቀችው በላይ ነበር ።

---

8፥13 ፡- ዘጸ. 23፥14-17 ፤ 34፥22-23 ፤ ዘኍ. 28፥9 ፡ 29፥39 ፤ ዘዳ. 16፥16 ። 9፥1-9 ፡- ማቴ. 12፥42 ፤ ሉቃ. 11፥31 ።

6 ንጉሥ ሮብዓምና የይሁዳ መሪዎችም ኃጢ
አት መሥራታቸውን በማመን “እግዚአብሔር
የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክል ነው” አሉ ።
7 እግዚአብሔርም ራሳቸውን እንዳዋረዱ ባየ
ጊዜ ነቢዩ ሸማዕያን እንደገና እንዲህ አለው ፤
“እነሆ በደላቸውን አምነው ራሳቸውን ስላዋ
ረዱ አላጠፋቸውም ፤ ሺሻቅ አደጋ በሚጥልባ
ቸው ጊዜ ፈጥኜ በመታደግ አድናቸዋለሁ ፤
በኢየሩሳሌምም ላይ ቊጣዬን ሙሉ በሙሉ
አላወርድም ፤ 8 ይሁን እንጂ በእኔ መገዛትና
በምድር ነገሥታት መገዛት መካከል ያለውን
ልዩነት ይገነዘቡ ዘንድ ሺሻቅ ድል አድርጎ ይገ
ዛቸዋል ።”
9 ስለዚህ ንጉሥ ሺሻቅ በድል አድራጊነት
ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶ በቤተ መቅደስና በቤተ
መንግሥት የነበረውን ሀብት ሁሉ ፤ ንጉሥ ሰሎ
ሞን ከወርቅ ያሠራቸውን ጋሻዎች ጭምር
ዘርፎ ወሰደ ፤ 10 ንጉሥ ሮብዓም ሺሻቅ በወሰዳ
ቸው ጋሻዎች ምትክ ሌሎች ጋሻዎችን ከነሐስ
አሠርቶ የቤተ መንግሥቱን ቅጽር በሮች በሚጠ
ብቁ የዘበኞች አለቆች ኀላፊነት እንዲቀመጡ
አደረገ ፤ 11 ንጉሡ ወደ ቤተ መቅደስ በመጣ
ቊጥር ዘበኞቹ እነዚህን ጋሻዎች አንግበው
ያጅቡታል ፤ ንጉሡ ከሄደ በኋላም መልሰው
በዘበኞች ክፍል ውስጥ ያኖሩአቸው ነበር ፤
12 ንጉሥ ሮብዓም በደሉን አምኖ ራሱን ስላዋ
ረደ የእግዚአብሔር ቊጣ ሙሉ በሙሉ ጒዳት
አላደረሰበትም ፤ እንዲያውም በይሁዳ ሁሉ
ነገር መልካም ሆነ ።

### የሮብዓም ዘመነ መንግሥት ታሪክ ባጭሩ

13 ሮብዓም መኖሪያውን እግዚአብሔር
ይመለክባት ዘንድ ከመላው የእስራኤል ግዛት
መካከል በመረጣት በኢየሩሳሌም ከተማ አድ
ርጎ ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ ፤ የመንግሥቱ
ንም ሥልጣን አጠናከረ ፤ እርሱም በነገሠ ጊዜ
ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር ፤ የሮብ
ዓም እናት ናዕማ ተብላ የምትጠራ የሀሞን
አገር ተወላጅ ነበረች ፤ 14 ሮብዓም የእግዚአብ
ሔርን ፈቃድ ለማወቅ ጥረት ባለማድረጉ ክፉ
ነገር ሠራ ።
15 ንጉሥ ሮብዓም ያደረገው ነገር ሁሉ ከመ
ጀመሪያ አስከ መጨረሻ እንዲሁም የቤተሰቡ
ታሪክ በነቢዩ ሸማዕያና በነቢዩ ዒዶ ታሪክ መጻ
ሕፍት ተመዝግቦ ይገኛል ፤ ሮብዓምና ኢዮርብ
ዓም ባለማቋረጥ በወትር ይዋጉ ነበር ፤ 16 ሮብ
ዓም ሞተ ፤ በዳዊት ከተማ በሚገኘው በነገሥ
ታት መካነ መቃብርም ተቀበረ ፤ በእርሱም
እግር ተተክቶ ልጁ አቢያ ነገሠ ።

## ምዕራፍ 13

### አቢያ በኢዮርብዓም ላይ ያደረገው ጦርነት
(1 ነገ. 15፥1-8)

1 ኢዮርብዓም በእስራኤል ላይ በነገሠ በዐ
ሥራ ስምንተኛው ዓመት ፤ አቢያ የይሁዳ
ንጉሥ ሆነ ፤ 2 መኖሪያውንም በኢየሩሳሌም
አድርጎ ሦስት ዓመት ነገሠ ፤ እናቱ ሚካያ
ተብላ የምትጠራ የጊብዓ ከተማ ተወላጅ የሆነ
የኡሪኤል ልጅ ነበረች ።
በአቢያና በኢዮርብዓም መካከል የከረረ ጦር
ነት ተነሥቶ ነበር ፤ 3 በዚህ ጊዜ አቢያ አራት
መቶ ሺ ሠራዊት ይዞ ሲዘምት ፤ ኢዮርብዓም
ደግሞ ስምንት መቶ ሺ ወታደሮችን አሰልፎ
ጦርነት ገጠመው ።
4 ከዚህ በኋላ አቢያ ኰረብታማ በሆነ በኤፍ
ሬም አገር ወደሚገኘው ወደ ጽማራይም ተራራ
ወጥቶ ቆመ ፤ ድምፁን ከፍ በማድረግም ለኢዮ
ርብዓምና ለእስራኤላውያን በሙሉ እንዲህ
አለ ፤ “እነሆ አድምጡኝ! 5 ዳዊትና ዝርያዎቹ
በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንደሚነግሡ የእስራ
ኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር
የማይሻር ቃል ኪዳን መግባቱን አታውቁምን?
6 ይህ ሆኖ ሳለ የሰሎሞን አሽከር የሆነው የናባጥ
ልጅ ኢዮርብዓም በጌታው በሰሎሞን ላይ
ዐመፀ ፤ 7 ዘግየት ብሎም ኢዮርብዓም የማይረቡ
ወሮበሎችን ሰበሰበ ፤ እነርሱም በዕድሜው ማነ
ስና በዕውቀት ያልበሰለ በመሆኑ ሊቋቋማቸው
የማይችለውን የሰሎሞንን ልጅ ሮብዓምን ተቃ
ወሙት ፤ 8 አሁንም እናንተ እግዚአብሔር ለዳ
ዊት ዝርያዎች የሰጠውን የመንግሥት ሥልጣን
በመድፈር ለመቃወም አቅዳችኋል ፤ ይህ ዕቅዳ
ችሁ ግቡን እንዲመታ ለማድረግም እጅግ ብዙ
የሆነ የጦር ሠራዊት አሰልፋችኋል ፤ ለእናንተ
አማልክት እንዲሆኑ ኢዮርብዓም ከወርቅ ያሠራ
ቸውን የኰርማ ምስሎች ይዛችሁ መጥ
ታችኋል ። 9 የእግዚአብሔር ካህናት የሆኑትን
የአሮንን ዝርያዎችና ሌዋውያንን አባረራችሁ ፤
በእነርሱም ምትክ ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደ
ርጉት ሁሉ ለራሳችሁ ካህናትን ሾማችኋል ፤
አንድ ኰርማ ወይም ሰባት በጎች ይዞ ወደ እና
ንተ የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ሐሰተኞች
ለሆኑት አማልክቶቻችሁ ካህን አድርጋችሁ
ትሾማላችሁ ።
10 “እኛ ግን አሁንም እግዚአብሔር አምላካ
ችንን እናመልካለን ፤ ከእርሱም ፈቀቅ አላል
ንም ፤ የአሮን ዝርያዎች የሆኑ ካህናትም እግዚ
አብሔርን ማገልገላቸውን አላቋረጡም ፤ ሌዋው
ያንም እንደ ወትሮው ሁሉ ካህናትን ይረዳሉ ፤
11 በየቀኑ ጠዋትና ማታ ዕጣንና ሙሉ በሙሉ

12፥9 ፦ 1ነገ. 10፥16-17 ፤ 2ዜ.መ. 9፥15-16 ።

ዐይነት ስጦታ ለንጉሥ ኢዮሣፍጥ ቢያበረክቱ፥
አንዳንድ ዐረቦች ደግሞ ሰባት ሺ ሰባት መቶ
በጎችና ሰባት ሺ ሰባት መቶ ፍየሎች አመጡ
ለት፤ 12-13 ስለዚህ ኢዮሣፍጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ
ይበልጥ ገናና እየሆነ ሄደ፤ በመላው ይሁዳ
ምሽጎችንና ፥ እጅግ የበዛ ስንቅና ትጥቅ የተከማ
ቹባቸውን ከተማዎች ሠሩ።
በኢየሩሳሌምም የተለየ ችሎታ ያላቸውን
የጦር መኰንኖች አሰለፈ ነበር፤ 14 ከይሁዳ
ነገድ ጐሳዎች ለተመለመሉት ወታደሮች አዛዥ
ዐድና ተብሎ የሚጠራ የጦር መኰንን ነበር፤
በእርሱም ሥር ሦስት መቶ ሺ ወታደሮች
ነበሩ፤ 15 ከእርሱም ቀጥሎ በማዕርግ ሁለተኛ
የሆነው የሆሐናን ተብሎ የሚጠራ የጦር አዛዥ
ነበር፤ በእርሱም ሥር ሁለት መቶ ሰማኒያ ሺ
ወታደሮች ነበሩ፤ 16 ከየሆሐናን ቀጥሎ በማዕ
ርግ ሦስተኛ የሆነው የጦር መኰንን የዚክሪ
ልጅ ዐማስያ ነበር፤ በእርሱም ሥር ሁለት
መቶ ሺ ወታደሮች ነበሩ፤ እርሱም በገዛ
ፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የለየ
የጦር አዛዥ ነበር፤ 17 ከብንያም ነገድ ጐሳዎች
ለተመለመሉት ወታደሮች ዋና አዛዥ ኤሊያዳዕ
ተብሎ የሚጠራ ተወዳዳሪ የሌለው ጀግና ወታ
ደር ነበር፤ በእርሱም ሥር ጋሻና ቀስት የያዙ
ሁለት መቶ ሺ ወታደሮች ነበሩ፤ 18 ከእርሱ
ቀጥሎ በማዕርግ ሁለተኛ የሆነው የሆዛባድ
ተብሎ የሚጠራ የጦር አዛዥ ነበር፤ በእርሱም
ሥር ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ አንድ መቶ ሰማኒያ
ሺ ወታደሮች ነበሩ፤ 19 እነዚህ ሁሉ ወታደሮች
ንጉሥ ኢዮሣፍጥን በኢየሩሳሌም የሚያገለግሉ
ሲሆኑ ፥ በተጨማሪም ንጉሡ በሌሎቹ በተመሸ
ጉት የይሁዳ ከተማዎች ሌሎች ወታደሮችን
አሰፍሮ ነበር።

## ምዕራፍ 18

### ነቢዩ ሚካያ ንጉሥ አክአብን አስጠነቀቀ
(1 ነገ. 22፥1-28)

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በሀብት በበለጸ
ገና ዝነኛ በሆነ ጊዜ የእርሱና የእስራኤል
ንጉሥ አክአብ ቤተሰብ በጋብቻ እንዲተሳሰሩ
አደረገ፤ 2 ከጥቂት ዓመታት በኋላም ኢዮሣፍጥ
አክአብን ለመጐብኘት ወደ ሰማርያ ከተማ
ሄደ፤ አክአብም ለኢዮሣፍጥና ለአጃቢዎቹ
ክብር ብዙ በጎችንና የቀንድ ከብቶችን ዐርዶ
ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ አክአብ በገለዓድ በሚገ
ኘው በራሞት ከተማ ላይ አደጋ ለመጣል ይተባ
በረው ዘንድ ኢዮሣፍጥን ለማግባባት በመሞ
ከር ፥ 3 "በራሞት ላይ አደጋ ለመጣል ከእኔ
ጋር ትዘምታለህን?" ሲል ጠየቀው።
ኢዮሣፍጥም "አንተ ከተዘጋጀህ እኔም
ሆንሁ ሠራዊቴ ዝግጁ ነን፤ እንተባበርሃማለን፤
4 ነገር ግን አስቀድመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ
እንጠይቅ" አለው።

5 ስለዚህ አክአብ ቍጥራቸው አራት መቶ
የሆነውን የራሱን ነቢያት ጠርቶ "ወደ ራሞት
ሄጄ አደጋ ልጣልባት ወይስ ልተው?" ሲል
ጠየቃቸው።
እነርሱም "ሄደህ አደጋ ጣልባት፤ እግዚአብ
ሔርም ድልን ያቀዳጅሃል" ሲሉ መለሱለት።
6 ኢዮሣፍጥ ግን "በእርሱ አማካይነት የእግ
ዚአብሔርን ፈቃድ የምንጠይቅበት ሌላ ነቢይ
በዚህ የለምን?" ሲል ጠየቀ።
7 አክአብም "የይምላ ልጅ የሆነ ሚካያ
ተብሎ የሚጠራ ሌላም ነቢይ አለ፤ ነገር ግን
እርሱን አልወድደውም፤ ምክንያቱም እርሱ
ምንጊዜም ቢሆን ስለ እኔ ክፉ እንጂ መልካም
የትንቢት ቃል መናገር አይፈቅድም" ቢል
መለሰለት።
ኢዮሣፍጥም "አንተ ይህን ማለት አይገባ
ህም" አለው።
8 ከዚህ በኋላ ንጉሥ አክአብ ባለሟሎቹ ከሆ
ኑት ባለሥልጣኖች አንዱን ጠርቶ "ሚካያን
ፈልገህ በማግኘት በፍጥነት እንዲመጣ አድ
ርግ" ሲል አዘዘው።
9 በዚህ ጊዜ ሁለቱ ነገሥታት ልብሰ መንግ
ሥታቸውን ለብሰው በሰማርያ ቅጽር በር አጠ
ገብ በውጪ በኩል በሚገኘው አውድማ በየዙፋ
ናቸው ላይ ተቀምጠው ነበር፤ ነቢያቱም ሁሉ
በነገሥታቱ ፊት ሆነው የትንቢት ቃል ይናገሩ
ነበር፤ 10 ከእነርሱም አንዱ የከናዕና ልጅ ጺድ
ቂያ ከብረት ቀንዶችን ሠርቶ አክአብን "እግዚ
አብሔር 'በእነዚህ ቀንዶች ሶርያውያንን መግ
ተህ ፍጹም የሆነ ድልን ትቀዳጃለህ' ይልሃል"
አለው። 11 ሌሎቹም ነቢያት ይህንኑ ቃል በመ
ደገፍ "በራሞት ላይ ዝመት፤ ታሸንፋለህ፤ እግ
ዚአብሔር ድልን ይሰጥሃል" አሉት።
12 ሚካያን ለመጥራት ሄዶ የነበረው መልእ
ክተኛ በዚሁ ጊዜ ሚካያን "ሌሎች ነቢያት
በሙሉ ንጉሥ አክአብ ድል የሚያደርግ መሆ
ኑን የሚያረጋግጥ የትንቢት ቃል ተናግረዋል፤
ስለዚህ አንተም እንደነርሱ ብታደርግ ይሻል
ሃል" አለው።
13 ሚካያ ግን "እግዚአብሔር የሚገልጥል
ኝን ቃል ብቻ የምናገር መሆኔን በሕያው እግዚ
አብሔር ስም እምላለሁ" ሲል መለሰለት።
14 ሚካያም ወደ ንጉሥ አክአብ ፊት በቀረበ
ጊዜ ንጉሡ "ሚካያ ሆይ! ንጉሥ ኢዮሣፍጥና
እኔ ወደ ራሞት ሄደን አደጋ እንጣልባት ወይስ
እንተው?" ሲል ጠየቀው።
ሚካያም "ዘምተህ አደጋ ጣልባት! በእርግ
ጥም ታሸንፋለህ፤ እግዚአብሔርም ድልን ያቀ
ዳጅሃል" ቢል መለሰለት።
15 አክአብም "አንተ በእግዚአብሔር ስም
የትንቢት ቃል ስትናገረኝ እውነቱን ተናገር!
እውነቱን እንድትነግረኝ ስንት ጊዜ ነው የምነ
ግርህ?" አለው።

አብረው ይሂዱ ፤ ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት
የሚሞክር ማንኛውም ሰው ይገደል ።”
8 ሌዋውያንና የይሁዳ ሕዝብ ካህኑ ዮዳሄ
የሰጣቸውን መመሪያ ሁሉ ፈጸሙ ፤ ዮዳሄም
አገልግሎታቸውን ፈጽመው በሰንበት ቀን
ከሥራ ነፃ መሆን የሚገባቸው ሌዋውያን አላሰ
ናበታቸውም ነበር ፤ ስለዚህ ለዘብ ጥበቃ የሚሠ
ማሩትና ከዘብ ጥበቃ ነፃ የሆኑት እዚያው ሰለነ
በሩ የጦር መኰንኖቹ በቂ ሰዎች ነበሩአቸው ፤
9 ዮዳሄም በቤተ መቅደስ ተጠብቀው ይኖሩ የነ
በሩትን የንጉሥ ዳዊትን ጦሮችና ጋሻዎች
ለጦር መኰንኖቹ ሰጣቸው ፤ 10 ጭፍሮቹም
ሁሉ ሰይፋቸውን እንደመዘዙ ንጉሡን ከአደጋ
ለመከላከል በመሠዊያው በኩል በቤተ መቅደሱ
ፊት ለፊት ዙሪያውን ተሰልፈው እንዲቆሙ
አደረጋቸው ። 11 ከዚህ በኋላ ዮዳሄ ኢዮአስን
አውጥቶ በራሱ ላይ ዘውድ ጫነበት ፤ ስመንግ
ሥቱ መመሪያ የሆነውንም ሕግ አንድ ቅጅ አስ
ረከበው ፤ በዚህ ዐይነት ሁኔታም ካህኑ ዮዳሄና
ልጆቹ ኢዮአስን ቀብተው አነገሡት ፤ ሕዝቡም
ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው “ንጉሡ ለዘላ
ለም ይኑር !” በማለት ደስታቸውን ገለጡ ።
12 ሀታልያ ሕዝቡ ለንጉሡ ያደረገውን እል
ልታና ሆታ ሰምታ ሕዝቡ ወደ ተሰበሰበበት
ወደ ቤተ መቅደስ በፍጥነት መጣች ፤ 13 እዚ
ያም እንደደረሰች አዲሱ ንጉሥ በተለመደው
ባሕል መሠረት ለነገሥታት በተመደበው በቤተ
መቅደሱ መግቢያ በሚገኘው ዐምድ አጠገብ
በጦር መኰንኖችና በመለከት ነፊዎች ተከብቦ
ታጅቦ እንደቆመ አየች ፤ ሕዝቡም በደስታ
ተሞልተው እልል ይሉ ነበር ፤ መለከት ነፊዎ
ችም መለከት ይነፉ ነበር ፤ የቤተ መቅደስ መዘ
ምራንም በሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅበው የበዓ
ሉን ሥነ ሥርዓት ይመሩ ነበር ፤ ሀታልያም
በድንጋጤ ልብሰዋን በመቅደድ “ይህ ሤራ
ነው ! ይህ ሤራ ነው !” ስትል ጮኸች ።
14 ዮዳሄ በበኩሉ ዐታልያ በቤተ መቅደሱ
ክልል ውስጥ እንድትገደል አልፈለገም ፤ ስለዚ
ህም የጦር መኰንኖቹን ጠርቶ “ግራና ቀኝ
በተሰለፉት ዘቦች መካከል አውጥታችሁ ውሰዱ
አት ፤ እርስዋን ከሞት ለማትረፍ የሚሞክር
ሰው ቢኖር ግደሉት” ሲል አዘዛቸው ።
15 እነርሱም እርስዋን አፈፍ አድርገው በመ
ያዝ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱአት ፤ እዚያም
“የፈረስ መግቢያ ቅጽር በር” ተብሎ በሚጠ
ራው ስፍራ ገደሉአት ።

### ዮዳሄ ያደረገው መሻሻል
(2 ነገ. 11፥17-20)

16 ካህኑ ዮዳሄ ራሱ እንዲሁም ንጉሥ ኢዮአ
ስና ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸውን
ለማደስ ቃል ኪዳን እንዲገቡ አደረገ ። 17 ከዚ
ህም በኋላ ሁሉም በአንድነት ባዓል ተብሎ
ወደሚጠራው የጣዖት ማምለኪያ ቤት ሄደው
አፈረሱት ፤ መሠዊያዎቹንና ምስሎቹን ሁሉ
ሰባበሩ ፤ ማታን ተብሎ የሚጠራውንም የባዓል
ካህን በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት ገደሉት ።
18 ዮዳሄ ካህናቱንና ሌዋውያኑን የቤተ መቅ
ደሱ ሥራ ኀላፊዎች እንዲሆኑ አደረገ ፤ የእነር
ሱም ተግባር በንጉሥ ዳዊት የተመደበላቸውን
ሥራ ማከናወንና በሙሴ ሕግ መሠረት ለእግዚ
አብሔር የሚቀርቡትን መሥዋዕት ማቃጠል
ነበር ፤ እንዲሁም በዳዊት መመሪያ መሠረት
የሙዚቃና የበዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ኀላፊ
ነት ተሰጥቶአቸው ነበር ፤ 19 ዮዳሄ በሕጉ መሠ
ረት ያልነጻ ማንኛውም ሰው ወደ ቤተ መቅደስ
እንዳይገባ በቤተ መቅደሱ ቅጽር በሮች ሆነው
የሚጠብቁ ዘበኞችን መድቦ ነበር ።
20 የጦር መኰንኖቹ ፥ የታወቁ የአገር ሽማግ
ሌዎች የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የቀሩትም
ሕዝብ ሁሉ ከዮዳሄ ጋር በመሆን ከቤተ መቅ
ደስ እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ ንጉሡን አጅ
በው ሄዱ ፤ በቤተ መንግሥቱም ዋና በር ገቡ ፤
ንጉሡም በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ ፤ 21 ሕዝቡም
ሁሉ በታላቅ ደስታ ተሞሉ ፤ ሀታልያም ተገ
ድላ ስለነበር ከተማይቱ ሰላም ሰፍኖባት ጸጥ
ብላ ነበር ።

## ምዕራፍ 24

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ
(2 ነገ. 12፥1-16)

1 ኢዮአስ በሰባት ዓመቱ የይሁዳ ንጉሥ
ሆነ ፤ መኖሪያውንም በኢየሩሳሌም አድርጎ
አርባ ዓመት ገዛ ፤ እናቱም ጺቢያ ተብላ የምት
ጠራ የቤርሳቤህ ከተማ ተወላጅ ነበረች ፤
2 ካህኑ ዮዳሄ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ
ኢዮአስ ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር
ያደርግ ነበር ፤ 3 ዮዳሄ ለንጉሥ ኢዮአስ ሁለት
ሚስቶችን መርጦለት ነበር ፤ እነርሱም ወንዶች
ንና ሴቶች ልጆችን ወልደውለታል ።
4 ኢዮአስ ከነገሠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቤተ
መቅደሱን ለማደስ ወሰነ ፤ 5 ስለዚህ ካህናቱንና
ሌዋውያኑን በአንድነት ሰብስቦ “ወደ ይሁዳ
ከተማዎች ሂዱና ለቤተ መቅደሱ ዓመታዊ
ዕድሳት የሚሆን በቂ ገንዘብ ከእስራኤል ሕዝብ
ሁሉ በፍጥነት ሰብስቡ” ሲል አዘዛቸው ፤ ሌዋ
ውያኑ ግን ቸል በማለት ዘገዩ ፤ 6 ስለዚህ ንጉሥ
ኢዮአስ የሌዋውያኑን መሪ ዮዳሄን ጠርቶ ፥
“የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ፥ እግዚአብ
ሔር ለሚመለክበት ድንኳን አገልግሎት የሚ
ሆን ግብር የእስራኤል ሕዝብ እንዲያዋጣ ያዘዘ
ውን ሌዋውያኑ ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ሕዝብ

24፥6 ፦ ዘጸ. 30፥11-16 ።

[26]በአካዝ ዘመን መንግሥት ከመጀመሪያ
እስከ መጨረሻ የተፈጸመው ሌላው ነገር ሁሉ
በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጻሕ
ፍት ተመዝግቦ ይገኛል፤ [27]ንጉሥ አካዝ
ሞተ፤ በኢየሩሳሌምም ተቀበረ፤ ይሁን እንጂ
በነገሥታት መካነ መቃብር አልተቀበረም፤ በእ
ርሱም እግር ተተክቶ ልጁ ሕዝቅያስ ነገሠ።

## ምዕራፍ 29

### የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ

(2 ነገ. 18፥1-3)

[1]ሕዝቅያስ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ሲሆነው ነገሠ፤ መናገሪያውንም በኢየሩሳሌም
አድርጎ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ፤ እናቱ አቢያ
ተብላ የምትጠራ የዘካርያስ ልጅ ነበረች፤
[2]ሕዝቅያስ የቀድሞ አባቱን የንጉሥ ዳዊትን
መልካም ምሳሌነት በመከተል እግዚአብሔርን
ደስ የሚያሰኝ ነገር አደረገ።

### የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደገና የመንጻት ተግባር

[3]ሕዝቅያስ በነገሠበት ዓመት በመጀመሪያው
ወር የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በር ሁሉ
እንደገና ከፍቶ አደሰ፤ [4]ካህናትንና ሌዋውያንን
በስተ ምሥራቅ በኩል በሚገኘው በቤተ መቅ
ደሱ አደባባይ ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፦ [5]"እና
ንተ ሌዋውያን ራሳችሁን መቀደስና የቀድሞ
አባቶቻችሁ አምላክ የሆነውን የእግዚአብሔርን
ቤተ መቀደስ ማንጻት አለባችሁ፤ ቤተ መቅደ
ሱን የሚያረክስ ነገር ሁሉ ከቤተ መቅደሱ ማስ
ወገድ ይኖርባችኋል። [6]የቀድሞ አባቶቻችን
ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የነበራቸውን ታማ
ኝነት በማጉደል አሳዘኑት፤ እርሱንም በመተው
የእርሱ መኖሪያ ከሆነው ስፍራ ፊታቸውን
አዞሩ፤ [7]የቤተ መቅደሱን በር ሁሉ ዘጉ፤ መብ
ራቶቹንም አጠፉ፤ የእስራኤል አምላክ በሆነው
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ዕጣንን
ማጠን ወይም መሥዋዕትን ማቅረብ ተዉ፤
[8]በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቊጣ በይ
ሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ወረደ፤ በእነርሱም
ላይ የወረደው መቅሠፍት ሁሉንም የሚያስደነ
ግጥና የሚያስፈራ ሆነ፤ እናንተም ይህን ሁሉ
በሚገባ ታውቃላችሁ፤ [9]አባቶቻችን በጦርነት
ተገድለዋል፤ ሚስቶቻችንና ልጆቻችን ሁሉ
እስረኞች ሆነው ተወስደዋል።
[10]"ከአንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር ቊጣ
በእኛ ላይ እንዳይወርድብን እነሆ እኔ አሁን
የእስራኤል አምላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር
ጋር ቃል ኪዳን ለመግባት ወስኛለሁ፤
[11]ልጆቼ ሆይ! እንግዲህ ቸልተኞች አትሁኑ!
ምክንያቱም እናንተ ዕጣን እንድታጥኑለትና
ሕዝቡ እርሱን በማምለክ የሚፈጽመውን ሥነ
ሥርዓት እንድትመሩለት እግዚአብሔር የመረጣ
ችሁ ናችሁ።"
[12-14]ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘረው
ሌዋውያን በዚያ ነበሩ፦

ከቀሃት ጐሳ፦ የዐማሣይ ልጅ ማሐትና
 የዐዛርያስ ልጅ ኢዩኤል፤
ከመራሪ ጐሳ፦ የዓብዲ ልጅ ቂሽና
 የይሀልኤል ልጅ ዐዛርያስ፤
ከጌርሾን ጐሳ፦ የዚማ ልጅ ዮአሕና
 የዮአሕ ልጅ ዔዴን፤
ከኤሊጻፋን ጐሳ፦ ሺምሪና ይዒኤል፤
ከአሳፍ ጐሳ፦ ዘካርያና ማታንያ፤
ከሄማን ጐሳ፦ ይሒኤልና ሺምዒ፤
ከይዱቱን ጐሳ፦ ሸማዕያና ዑዚኤል።

[15]እነዚህም ሰዎች ሌዋውያን ወገኖቻቸውን
ሰብስበው ሁሉም በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት
ራሳቸውን በሥርዓት አነጹ፤ ከዚህም በኋላ
ንጉሡ እንዳዘዛቸው ሌዋውያኑ በእግዚአብሔር
ሕግ መሠረት ቤተ መቅደሱን በሥርዓት
አነጹ፤ [16]ካህናቱም ቤተ መቅደሱን ለማንጻት
ወደ ውስጡ ገቡ፤ በሕጉ መሠረት በሥርዓት
ያልነጻውንም ነገር ሁሉ ወደ ቤተ መቅደሱ
አደባባይ አወጡት፤ ሌዋውያኑም ከዚያ አንሥ
ተው ከከተማ ውጭ በመውሰድ በቄድሮን ሸለቆ
ጣሉት።
[17]የማንጻቱ ሥራ በመጀመሪያው ወር
መባቻ ቀን ተጀምሮ በስምንተኛው ቀን ወደ
ቤተ መቅደስ የሚያስገባው ክፍል ጭምር
ሙሉ በሙሉ ተፈጸመ፤ ከዚህ በኋላም ቤተ
መቅደሱን ለአምልኮ ሥነ ሥርዓት ስማዘጋጀት
በተከታዮቹ ስምንት ቀኖች ማለትም ወሩ በገባ
እስከ ዐሥራ ስድስተኛው ቀን ድረስ ሠሩ።

### ቤተ መቅደሱ እንደገና ለእግዚአብሔር የተለየ ሆነ

[18]ሌዋውያኑ ስለተከናወነው ሥራ ለንጉሥ
ሕዝቅያስ የሚከተለውን መግለጫ አቀረቡ፦
"የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበትን መሠ
ዊያ፥ የተቀደሰው ኅብስት የሚቀመጥበትን ገበ
ታና ከእነርሱም ጋር የተያያዙትን ሌሎች ዕቃ
ዎች ጭምር ቤተ መቅደሱን በሙሉ በሕጉ
መሠረት በሥርዓት አንጽተናል፤ [19]እንዲሁም
ንጉሥ አካዝ ለእግዚአብሔር ታማኝ ባልነበረ
በት ዓመታት ወስዶት የነበረውን ዕቃ ሁሉ
መልሰን በማምጣት ለእግዚአብሔር የተለዩ እን
ዲሆኑ አድርገናል፤ እነዚህም ዕቃዎች በሙሉ
ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በሚቀርብበት መሠ
ዊያ ፊት ለፊት ባለው ስፍራ ይገኛሉ።"

28፥27፦ ኢሳ. 14፥28።

ከሆኑትም ሕዝቦች ሁሉ ጋር በሰላም እንዲኖሩ
ፈቀደ ፤ 23 ብዙ ሕዝብም ለእግዚአብሔር
መባን ፥ ለንጉሥ ሕዝቅያስ ደግሞ ገጸ በረከትን
ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ፤ ከዚያም ጊዜ
ጀምሮ ሕዝቦች ሁሉ ሕዝቅያስን ከፍ ባለ አክብ
ሮት ተመለከቱት ።

### የሕዝቅያስ መታመምና ዕብሪተኛነቱ
(2 ነገ. 20፥1-3፤12-19፤ ኢሳ. 38፥1-3፤ 39፥1-8)

24 በዚሁን ጊዜ ንጉሥ ሕዝቅያስ ታሞ
ሊሞት ተቃርቦ ነበር ፤ ወደ እግዚአብሔርም
ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም እንደሚያድነው የሚያ
ረጋግጥ ምልክት አሳየው ፤ 25 ሕዝቅያስ ግን
ልቡ በትዕቢት ተሞልቶ ስለነበር እግዚአብሔር
ስላደረገለት ቸርነት ሁሉ ተገቢ ምስጋና አላቀረ
በም ፤ ከዚህም የተነሣ በእርሱ ፥ በይሁዳና በኢ
የሩሳሌም ሕዝብ ቁጣ መቅሠፍት ደረሰባቸው ።
26 ይሁን እንጂ በመጨረሻ ሕዝቅያስና የኢየሩሳ
ሌም ሕዝብ በትሕትና ራሳቸውን ስላዋረዱ
ሕዝቅያስ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየበት
ጊዜ ድረስ እግዚአብሔር ሕዝቡን አልቀጣም ።

### የሕዝቅያስ ብልጽግናና ገናናነት

27 ንጉሥ ሕዝቅያስ እጅግ በለጸገ ፤ ሕዝቡም
ሁሉ አከበሩት ፤ ወርቁን ፥ ብሩን ፥ የከበረ
ዕንቊውን ፥ ቅመማ ቅመሙን ፥ ጋሻዎቹንና
ሌሎቹንም ውድ የሆኑ ዕቃዎቹን የሚያኖርባ
ቸው ዕቃ ግምጃ ቤቶችን ሠራ ፤ 28 በተጨማ
ሪም ለእህሉ ፥ ለወይን ጠጁና ለወይራ ዘይቱ
ማኖሪያ የሚሆኑ የዕቃ ግምጃ ቤቶችን ፥ ለቀንድ
ከብቶቹ በረት ፥ ለበጎቹም ጒረኖ ሠርቶ ነበር ፤
29 ከዚህም ሁሉ ሌላ እግዚአብሔር ብዙ የቀ
ንድ ከብትና የበግ መንጋ እንዲሁም ሌላ እጅግ
የበዛ ሀብት ስለሰጠው ብዙ ከተማዎችን ሠራ ፤
30 በላይ በኩል ያለውን የግዮንን ምንጭ
መውጫ ገድቦ ውሃውን በቦይ ወደ ኢየሩሳሌም
ምዕራብ ቅጽር ውስጥ እንዲወርድ ያደረገም
ሕዝቅያስ ነው ፤ ሕዝቅያስ ያደረገው ነገር ሁሉ
በመልካም ሁኔታ ተሳካለት ፤ 31 ነገር ግን የባቢ
ሎን መልእክተኞች በአገሪቱ ስለተደረገው አስ
ደናቂ ነገር ሊጠይቁት ወደ እርሱ መጥተው
በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቅያስ ልብ
ውስጥ ያለውን አሳብ ለማወቅ ይፈትነው ዘንድ
ተወው ።

### የሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ
(2 ነገ. 20፥20-21)

32 ንጉሥ ሕዝቅያስ ያደረገው ሌላው ነገር
ሁሉ ፥ ለእግዚአብሔርም የነበረው መንፈሳዊ
ቅንአት በዓሞጽ ልጅ በነቢዩ ኢሳይያስ ራእይ
እንዲሁም በይሁዳና በእስራኤል የታሪክ መጻሕ
ፍት ተመዝግበው ይገኛሉ ። 33 ሕዝቅያስ
ሞተ ፤ በላይኛው ክፍል በሚገኘውም በነገሥ
ታት መካነ መቃብር ተቀበረ ፤ የይሁዳና የኢየ
ሩሳሌም ሕዝብም ሁሉ ታላቅ የቀብር ሥነ
ሥርዓት አደረጉለት ፤ በእርሱም እግር ተተክቶ
ልጁ ምናሴ ነገሠ ።

## ምዕራፍ 33
### የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ
(2 ነገ. 21፥1-9)

1 ምናሴ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር ፤ መኖሪያውንም በኢ
የሩሳሌም አድርጎ ኀምሳ አምስት ዓመት ገዛ ፤
2 የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ አገር በሚገ
ቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ከፊታቸው ነቃቅሎ
ያጠፋቸውን የአሕዛብን አሳፋሪ ልማድ በመከ
ተል ምናሴ የሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርን
አሳዘነ ፤ 3 ምናሴ አባቱ ሕዝቅያስ አፈራርሶአ
ቸው የነበሩትን አረማውያን የማምለኪያ ስፍራ
ዎች እንደገና ሠራ ፤ ባዓል ተብሎ ለሚጠራው
ባዕድ አምላክ መሠዊያዎችን ፥ አሼራ ተብላ
ለምትጠራው ሴት አምላክ ምስሎችን አቆመ ፤
የሰማይ ከዋክብትንም አመለከ ፤ 4 እግዚአብሔር
ለዘላለም እንዲመለክበት ባዘዘው ስፍራ ፥ ማለ
ትም በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ አረ
ማዊ መሠዊያዎችን ተከለ ፤ 5 በሁለቱም የቤተ
መቅደሱ አደባባዮች የሰማይ ከዋክብት የሚመለ
ክባቸውን መሠዊያዎች ሠራ ፤ 6 የገዛ ወንዶች
ልጆቹንም በሂኖም ሸለቆ የሚቃጠል መሥዋ
ዕት አድርጎ አቀረበ ፤ እርሱም ራሱ ሟርተኛና
አስማተኛ ሆኖ ከጠንቋዮችና ከሙታን ጠሪዎች
ምክርን ይጠይቅ ነበር ፤ በዚህም ሁሉ አድራ
ጎቱ ታላቅ ኃጢአት ስለሠራ እግዚአብሔርን
አስቈጣ ። 7 በቤተ መቅደስም ውስጥ የጣዖት
ምስልን አቆመ ፤ ይህም ቤተ መቅደስ እግዚአብ
ሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰሎሞን "ይህ በኢየሩሳ
ሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ እኔ እመለከበት
ዘንድ ከዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ግዛት
ሁሉ የመረጥሁት የተቀደሰ ስፍራ ነው ፤ 8 የእስ
ራኤል ሕዝብ ትእዛዙን ቢጠብቁና ለአገልጋዩ
ለሙሴ የሰጠሁትንም ሕግ ቢፈጽሙ ፥ ለቀድሞ
አባቶቻቸው ከሰጠኋቸው ከዚህች ምድር ተባር
ረው እንዲወጡ አልፈቅድም" ሲል ነግሮአቸው
የነበረው ነው ። 9 ምናሴ የይሁዳንና የኢየሩሳሌ
ምን ሕዝብ ፥ የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ
አገር በሚገቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ከፊታ
ቸው እንዲባረሩ ያደረጋቸው ሕዝቦች ካደረጉት
ይበልጥ የከፋ ኃጢአት እንዲሠሩ አደረጋቸው ።

---

33፥2 ፦ ኦሪ. 15፥4 ። 33፥4 ፦ 2ዜ.መ. 6፥6 ። 33፥7-8 ፦ 1ነገ. 9፥3-5 ፤ 2ዜ.መ. 7፥12-18 ።

### ምናሴ በሠራው ኃጢአት ተጸጸተ

10 ምንም እንኳ እግዚአብሔር ምናሴንና
ሕዝቡን በብርቱ ያስጠንቀቃቸው ቢሆንም እነ
ርሱ መስማትን እምቢ አሉ፤ 11 ስለዚህም የአ
ሦር ሠራዊት ይሁዳን እንዲወርር እግዚአብሔር
ፈቀደ፤ ሠራዊቱም ምናሴን ማርኮ በአፍንጫው
መንጠቆ በማግባት በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢ
ሎን ወሰደው። 12 ምናሴ ሥቃይ በበዛበት ጊዜ
ራሱን በትሕትና በማዋረድ ወደ አምላኩ ወደ
እግዚአብሔር ተመለሰ፤ የእግዚአብሔርንም ዕር
ዳታ ለመነ፤ 13 እግዚአብሔርም የምናሴን
ጸሎት ሰማ፤ ወደ ኢየሩሳሌምም ተመልሶ እን
ደገና እንዲገዛ ፈቀደለት፤ በዚህም ምናሴ እግ
ዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን ተገነ
ዘበ።
14 ከዚህ በኋላ ምናሴ በዳዊት ከተማ በስተ
ምሥራቅ በኩል የሚገኘውን የውጭ ቅጽር
ቁመት ከፍ አድርጎ ሠራ፤ ይህም ቅጽር በሸለ
ቆው ውስጥ ከግዮን ምንጭ በስተ ምዕራብ
በኩል አንሥቶ በስተ ሰሜን እስከ ዓሣ ቅጽር
በር የሚደርስ ሲሆን፥ በከተማይቱ አጠገብ
የሚገኘውን ዖፌል ተብሎ የሚጠራውን ስፍራ
የሚያጠቃልል ነው፤ እንዲሁም ምናሴ በተመ
ሸጉት የይሁዳ ከተማዎች ሁሉ ለእያንዳንዳ
ቸው አንዳንድ የክፍለ ጦር አዛዥ መደበላ
ቸው፤ 15 ምናሴ ባዕዳን አማልክትንና እርሱ
ራሱ በዚያ አቁሞት የነበረውን የጣዖት ምስል
ከቤተ መቅደስ አወጣ፤ እንዲሁም በኢየሩሳ
ሌም ቤተ መቅደሱ በቆመበት ኮረብታና በሌሎ
ችም ስፍራዎች ላይ የነበሩትን የጣዖታት መሠ
ዊያዎች ሁሉ አስወገደ፤ እነዚህንም ሁሉ አን
ሥቶ ከከተማይቱ ውጭ ጣላቸው፤ 16 እግዚአብ
ሔር ይመለክበት የነበረውንም መሠዊያ በማደስ
በላዩ ላይ ለደኅንነት የሚቀርበውን የኅብረት
መሥዋዕትና የምስጋና መባን አቀረበ፤ የእስራ
ኤል አምላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ያመል
ኩም ዘንድ መላውን የይሁዳ ሕዝብ አዘዘ፤
17 ምንም እንኳ ሕዝቡ በሌሎቹ የማምለኪያ
ስፍራዎች ላይ መሥዋዕት ማቅረባቸውን ቢቀጥ
ሉም፥ መሥዋዕቱን የሚያቀርቡት ለእግዚአብ
ሔር ብቻ ነበር።

### የምናሴ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ
(2 ነገ. 21፥17-18)

18 ምናሴ ያደረገው ሌላ ነገር ሁሉ፥ ለአም
ላኩ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት፥ ነቢያት
የእስራኤል አምላክ በሆነው በእግዚአብሔር
ስም ለምናሴ የተናገሩአቸው ቃላት ጭምር በእ
ስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝግ
በው ይገኛሉ፤ 19 ንጉሥ ምናሴ ወደ እግዚአብ
ሔር ያቀረበው ጸሎትና፥ እግዚአብሔርም ለጸ
ሎቱ የሰጠው መልስ፥ ተጸጽቶ ንስሓ ከመግባቱ
በፊት ያደረገው ኃጢአት ሁሉ፥ ማለትም የፈጸ
መው ልዩ ልዩ ክፋት፥ እርሱ ራሱ የሠራቸው
አረማውያን ማምለኪያ ስፍራዎችና አሼራ
ተብላ የምትጠራው ሴት አምላክ ምስሎች፥
ያመልካቸው የነበሩ ጣዖታት ሁሉ በነቢያት
የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግበው ይገ
ኛሉ፤ 20 ምናሴ ሞተ፤ በቤተ መንግሥቱም
አጠገብ በሚገኘው ስፍራ ተቀበረ፤ በእርሱም
እግር ተተክቶ ልጁ አሞን ነገሠ።

### የይሁዳ ንጉሥ አሞን
(2 ነገ. 21፥19-26)

21 አሞን ዕድሜው ሃያ ሁለት ዓመት ሲሆ
ነው በይሁዳ ላይ ነገሠ፤ መኖሪያውንም በኢየሩ
ሳሌም አድርጎ ሁለት ዓመት ገዛ፤ 22 እርሱም
እንደ አባቱ እንደ ምናሴ ኃጢአት በመሥራት
እግዚአብሔርን አሳዘነ፤ አባቱ ያመልካቸው የነ
በሩትንም ጣዖታት አመለከ፤ መሥዋዕትንም
አቀረበላቸው፤ 23 አባቱ እንዳደረገው ሁሉ
ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ በማዋረድ ወደ
እግዚአብሔር አልተመለሰም፤ እንዲያውም ከአ
ባቱ ይበልጥ የከፋ ኃጢአት ሠራ።
24 የአሞን ባለሟሎች የሆኑት ባለሥልጣኖች
በእርሱ ላይ በማሤር በቤተ መንግሥቱ ውስጥ
ገደሉት፤ 25 የይሁዳም ሕዝብ የአሞንን ገዳዮች
ገድለው በእርሱ እግር ልጁን ኢዮስያስን አነ
ገሡ።

## ምዕራፍ 34

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ
(2 ነገ. 22፥1-2)

1 ኢዮስያስ በይሁዳ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ስምንት ዓመት ነበር፤ መኖሪያውንም በኢየሩሳ
ሌም አድርጎ ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ፤ 2 ኢዮስ
ያስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር አደ
ረገ፤ የቀድሞ አባቱን የንጉሥ ዳዊትን መል
ካም ምሳሌነት በመከተል የእግዚአብሔርን ሕግ
ሁሉ በጥንቃቄ ጠበቀ።

### ኢዮስያስ አረማውያን የማምለኪያ ስፍራዎችን አስወገደ

3 ኢዮስያስ በነገሠ በስምንተኛ ዓመቱ፥ ገና
ወጣት ሳለ የቀድሞ አባቱ የንጉሥ ዳዊት አም
ላክ የሆነውን እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመረ፤
ከአራት ዓመት በኋላም አረማውያን የማምለኪያ
ስፍራዎችን፥ አሼራ ተብላ የምትጠራ የሴት
አምላክ ምስሎችንና ሌሎችን ጣዖታት ሁሉ
ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ማስወገድ ጀመረ፤
4 በእርሱም ትእዛዝ የእርሱ ሰዎች ባዓል ተብሎ

34፥1 ፦ ኤር. 3፥6። 34፥4 ፦ 2ነገ. 21፥3፤ 2ዜ.መ. 33፥3።

የሚጠራው ጣዖት ይመለከባቸው የነበሩትን
መሠዊያዎችንና በእነርሱም አጠገብ የነበሩትን
ዕጣን የሚታጠንባቸውን መሠዊያዎች ሰባበሩ፤
አሼራ ተብላ የምትጠራውን የሴት አምላክ ምስ
ሎችንና ሌሎችንም ጣዖታት ሁሉ ትቢያ እስኪ
ሆኑ ድረስ አንከታከቱአቸው፤ ትቢያውንም ወስ
ደው ለእነዚያ ጣዖታት መሥዋዕት ያቀርቡ በነ
በሩ ሰዎች መቃብር ላይ በተኑት፤ 5 ኢዮስያስ
የእረማውያንን ካህናት ዐፅም ሁሉ እነርሱ ራሳ
ቸው ይሰግዱላቸው በነበሩት መሠዊያዎች ላይ
አቃጠላቸው፤ ይህን ሁሉ በማድረጉም ይሁዳና
ኢየሩሳሌም በሥርዓት እንደገና እንዲነጹ አደ
ረገ፤ 6 እስከ ሰሜን ንፍታሌም ድረስ ባሉ በም
ናሴ፥ በኤፍሬምና በስምዖን ግዛቶች በሚገኙ
ከተማዎች እንዲሁም በተደመሰሱት አካባቢዎ
ቻቸው ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸመ፤ 7 በመላው
የእስራኤል ግዛት የነበሩትን የጣዖታት መሠዊያ
ዎችንና የአሼራ ምስሎችን ሁሉ ሰባበራቸው፤
ጣዖታቱንም ትቢያ እስኪሆኑ አደቀቃቸው፤
ዕጣን የሚታጠንባቸውንም የጣዖት መሠዊያ
ዎች አንኰታኰቶ ጣለ፤ ከዚህም በኋላ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ተመለሰ።

### የእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ተገኘ
(2 ነገ. 22፥3-20)

8 ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው
ዓመት የእረማውያንን አምልኮ በማጥፋት ምድ
ሪቱንና ቤተ መቅደሱን ካነጻ በኋላ፥ የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ ያድሱ ዘንድ የአጸልያን
ልጅ ሳፋንን፥ የኢየሩሳሌም አስተዳዳሪ የሆነ
ውን ማዕሤያንና ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነውን
የኢዮአሐዝን ልጅ ጸሐፊውን ዮአሕን በአጠቃ
ላይ ሦስት ሰዎችን ላከ፤ 9 ዘብ ጠባቂዎች የሆኑ
ሌዋውያን በቤተ መቅደስ ውስጥ የሰበሰቡት ገን
ዘብ ሁሉ ለሊቀ ካህናቱ ለሒልቂያ ተሰጠ፤ ገን
ዘቡም የተሰበሰበው ከኤፍሬም፥ ከምናሴና ከቀ
ሩትም የእስራኤል ሕዝብ፥ እንዲሁም ከይ
ሁዳ፥ ከብንያምና ከኢየሩሳሌም ሕዝብ ነበር፤
10 ይህም ገንዘብ ለቤተ መቅደሱ ዕድሳት ኀላፊ
ዎች ለነበሩት ለነዚያ ሦስት ሰዎች ተሰጠ፤ እነ
ርሱም በበኩላቸው ገንዘቡን ለሠራተኞችና
11 የይሁዳ ነገሥታት እንዲፈራርሱ ያደረጉአቸ
ውን ሕንጻዎች ማሠሪያ የሚሆን ድንጋይና እን
ጨት ይገዙበት ዘንድ ለአናጢዎችና ለግንበኞች
ሰጡ፤ 12 አናጢዎቹና ግንበኞቹም ሥራውን
በታማኝነት አከናወኑ፤ የእነርሱም የበላይ ተቈ
ጣጣሪዎች ከመራሪ ጐሳ ያሐትና ዖባድያ፥ ከቀ
ሃት ጐሳ ዘካርያስና መሹላም ተብለው የሚጠ
ሩት አራት ሌዋውያን ነበሩ፤ (ሌዋውያን ሁሉ
በሙዚቃ መሣሪያ የመሀመር ከፍ ያለ ችሎታ
ያላቸው ሰዎች ነበሩ፤) 13 ሌሎቹ ሌዋውያን
ዕቃዎችን ለሚያጓጉዙና በልዩ ልዩ ሥራ ለተ
መደቡ ሠራተኞች የበላይ ኀላፊዎችና ተቈጣጣ
ሪዎች ሲሆኑ፥ የቀሩት ሌዋውያን ደግሞ ጸሐፊ
ዎች ወይም ዘብ ጠባቂዎች ነበሩ።

14 የቀረበውን ገንዘብ ከግምጃ ቤት ያወጡ
በነበሩት ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ሒልቂያ እግዚአብ
ሔር ለሙሴ የሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ
መጽሐፍ አገኘ፤ 15 እርሱም ጸሐፊውን ሳፋንን
“የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ በዚህ በቤተ
መቅደሱ ውስጥ አግኝቻለሁ” በማለት መጽሐ
ፉን ሰጠው፤ 16 ሳፋንም መጽሐፉን ወደ
ንጉሡ ወስዶ ንጉሡን “እነሆ አንተ ያዘዝከንን
ሁሉ አድርገናል፤ 17 በቤተ መቅደሱ ተቀምጦ
የነበረውን ገንዘብ ወስደን ለሠራተኞችና እነር
ሱን ለሚቈጣጠሩ ሰዎች አስረክበናል” አለው፤
18 ንግግሩንም በመቀጠል “ሒልቂያ የሰጠኝ
መጽሐፍ እነሆ በእጄ ይገኛል” አለው፤ መጽ
ሐፉንም ለንጉሡ አነበበለት።

19 ንጉሡም መጽሐፉ ሲነበብለት በሰማ ጊዜ
በሐዘን ልብሱን ቀደደ፤ 20 ከዚህም በኋላ
ንጉሡ ለሒልቂያ፥ ለሳፋን ልጅ ለአሒቃም፥
ለሚካያ ልጅ ለዐብዶን፥ ለቤተ መንግሥቱ
ጸሐፊ ለሳፋንና የንጉሡ የቅርብ አገልጋይ ለሆ
ነው ለዐሳያ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጠ፥
21 “ሄዳችሁ ስለ እኔና እንዲሁም በእስራኤልና
በይሁዳ ስለቀረው ሕዝብ እግዚአብሔርን
ጠይቁ፤ በዚህ መጽሐፍ ስላለውም ትምህርት
አረጋግጡ፤ የቀድሞ አባቶቻችን ለእግዚአብ
ሔር ቃል ባለመታዘዛቸውና ይህ መጽሐፍ አድ
ርጉ የሚላቸውን ሁሉ ባለመፈጸማቸው እግዚአ
ብሔር ቍጣውን በእኛ ላይ አውርዶአል።”

22 ሒልቂያና የቀሩት ሰዎች ንጉሡ ባዘዛ
ቸው መሠረት በኢየሩሳሌም ከተማ አዲሱ
ክፍል ነዋሪ ወደሆነችው ሑልዳ ተብላ ወደም
ትጠራ ነቢይት ሄደው ስለተላኩበት ጉዳይ ጠየ
ቁአት፤ የዚህች ነቢይት ባለቤት ሻሉም ተብሎ
የሚጠራ የቲቅዋ ልጅ የሐርሐስ የልጅ ልጅ
ሲሆን፥ እርሱም የቤተ መቅደሱ አልባሳት
ኀላፊ ነበር፤ ሰዎቹም ለነቢይቱ ሁኔታውን በዝ
ርዝር ገለጡላት፤ 23 እርስዋም “ወደ እኔ ወደላ
ካችሁ ንጉሥ ተመልሳችሁ በመሄድ ከዚህ የሚ
ከተለውን የእግዚአብሔር ቃል ስጡት አለቻ
ቸው።” 24 ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር፥ “እኔ
እግዚአብሔር ለንጉሡ በተነበበለት መጽሐፍ
ውስጥ በሚገኙት እርግማኖች ኢየሩሳሌምንና
ሕዝብዋን ሁሉ እቀጣለሁ፤ 25 እነርሱ እኔን
ትተው ለባዕዳን አማልክት መሥዋዕት አቅርበ
ዋል፤ ይህም ያደረጉት በደል ቍጣዬን አነሣሥ
ቶአል፤ በኢየሩሳሌም ላይ የተነሣሣው ቍጣ
ዬም ይፈጸማል እንጂ አይበርድም፤ 26 ስለ
ንጉሡ የሆነ እንደሆነ፥ እኔ የእስራኤል አምላክ

34፥5 ፥- 1ነገ. 13፥2።

የሆንሁ እግዚአብሔር የምለው ይህ ነው፤
'አንተ በዚያ መጽሐፍ የተነገረውን ቃል ሰምተ
ሃል፤ 27 እኔ ኢየሩሳሌምንና ሕዝብዋን እንዴት
እንደምቀጣ በሰማህ ጊዜ ራስህን አዋርደህ በሐ
ዘን ልብስህን በመቅደድና በማልቀስ ንስሓ ገብ
ተሃል፤ ስለዚህ ጸሎትህን ሰምቼአለሁ፤
28 አንተ በሕይወት እስካለህ ድረስ በኢየሩሳ
ሌም ላይ ቅጣት አላመጣም፤ አንተ በሰላም
እንድትሞት አደርጋለሁ።' ”
ሰዎቹም ይህን መልእክት ይዘው ወደ
ንጉሥ ኢዮስያስ ተመለሱ።

### ኢዮስያስ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ቃል ኪዳን ገባ
(2 ነገ. 23፥1-20)

29 ንጉሥ ኢዮስያስ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን
የታወቁ ሽማግሌዎች ሁሉ በማስጠራት በአንድ
ነት እንዲሰበሰቡ አደረገ፤ 30 እነርሱም ከንጉሡ
ጋር ካህናትንና ሌዋውያንን፥ ሌሎችንም ሕዝብ
ማለትም ባለጸጎችንም ድኾችንም ሁሉ አስከት
ለው ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ፤ ንጉሡም በዚያ
ጠፍቶ በነበረውና በቤተ መቅደስ በተገኘው
የቃል ኪዳን መጽሐፍ የሰፈረውን ቃል በሙሉ
ለሕዝቡ አነበበ፤ 31 ኢዮስያስም ተነሥቶ በንጉሥ
ታቱ ዐምደ ወርቅ አጠገብ ቆመ፤ ለእግዚአብሔር
ታዛዥ ለመሆን፥ በፍጹም ልቡ፤ በፍጹም ነፍ
ሱም በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን
ሕግና ትእዛዝ ሁሉ ለመፈጸም ከእግዚአብሔር
ጋር ቃል ኪዳን ገባ፤ 32 ከዚህ በኋላ መላው የብን
ያም ሕዝብና በኢየሩሳሌም የተገኙ ሌሎች ሰዎች
ሁሉ ቃል ኪዳኑን ይጠብቁ ዘንድ ቃል እንዲገቡ
አደረገ፤ በዚህም መሠረት የኢየሩሳሌም ሕዝብ
የቀድሞ አባቶቻቸው አምላክ ከሆነው ከእግዚአ
ብሔር ጋር የገቡት ቃል ኪዳን የሚጠይቀውን
ግዴታ ሁሉ ፈጸሙ፤ 33 ንጉሥ ኢዮስያስ በእስራ
ኤል ግዛት ውስጥ የነበሩትን አስጸያፊ ጣዖታት
ሁሉ አስወግዶ ሕዝቡ አምላካቸውን እግዚአብ
ሔርን እንዲያገለግሉ አደረገ፤ በዘመነ መንግሥ
ቱም ሁሉ ሕዝቡ ከቀድሞ አባቶቻቸው አምላክ
ከእግዚአብሔር ፈቀቅ አላሉም።

## ምዕራፍ 35

### ኢዮስያስ የፋሲካን በዓል አከበረ
(2 ነገ. 23፥21-23)

1 ንጉሥ ኢዮስያስ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብ
ሔር ክብር የፋሲካን በዓል አከበረ፤ የመጀመሪ
ያው ወር በገባ በዐሥራ አራተኛው ቀን ሕዝቡ
የፋሲካን በግ ዐረዱ፤ 2 ካህናት በቤተ መቅደሱ
ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባር መደቡ በሚገባ
እንዲያካሄዱት አበረታታቸው፤ 3 እንዲሁም ራሳ
ቸውን ለእግዚአብሔር ለለዩ፥ የመላው እስራ
ኤል መምህራን ለሆኑ ሌዋውያን እንዲህ የሚል
መመሪያ ሰጠ፥ “የተቀደሰውን የቃል ኪዳን
ታቦት የዳዊት ልጅ ንጉሥ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ
መቅደስ ውስጥ አኑሩት፤ ከእንግዲህ ወዲህ እና
ንተ አምላካችሁ የሆነውን እግዚአብሔርንና ሕዝ
ቡን እስራኤልን ማገልገል እንጂ የቃል ኪዳኑን
ታቦት በትከሻችሁ ተሸክማችሁ ከስፍራ ወደ
ስፍራ መውሰድ የለባችሁም፤ 4 ንጉሥ ዳዊትና
ልጁም ንጉሥ ሰሎሞን በሰጡአችሁ ኀላፊነት
መሠረት በየጐሳችሁ በመመደብ በቤተ መቅደስ
አገልግሎት ቦታ ቦታችሁን ያዙ፤ 5 ከእናንተ አን
ዳንዶቹ ለየጐሳው ከተመደቡት ሌዋውያን ጋር
ሆናችሁ እያንዳንዱን የእስራኤል ሕዝብ ቤተሰብ
ለመርዳት በምትችሉበት ሁኔታ ራሳችሁን አደ
ራጁ፤ 6 ወገኖቻችሁ የሆኑ እስራኤላውያን እግዚ
አብሔር በሙሴ አማካይነት የሰጠውን መመሪያ
በጥንቃቄ ይከተሉ ዘንድ በሕጉ መሠረት ራሳች
ሁን አንጽታችሁ የፋሲካን በግ ዕረዱ።”
7 ንጉሥ ኢዮስያስ በዚያው በፋሲካ በዓል የተ
ገኙ ሕዝብ መሥዋዕት አድርገው የሚያቀርቡአ
ቸውን የራሱ ሀብት ከሆኑ የቀንድ ከብት፤ እንዲ
ሁም የበግና የፍየል መንጋ፥ ሠላሳ ሺ የበግና የፍ
የል ጥቦቶችንና ሦስት ሺ ኮርማዎችን ሰጠ፤ 8 የን
ጉሡ ባለሟሎች የሆኑ ባለሥልጣኖችም መሥዋ
ዕት ሆነው የሚቀርቡ እንስሳትን በገዛ ፈቃዳቸው
ለምዕመናን፥ ለካህናትና ለሌዋውያን ሰጡ፤
የቤተ መቅደሱ አለቆች የሆኑት ሊቀ ካህናቱ
ሒልቂያ፤ ዘካርያስና ይሒኤልም የፋሲካ መሥ
ዋዕት ሆነው የሚቀርቡ ሁለት ሺ ስድስት መቶ
የበግና የፍየል ጥቦቶችንና ሦስት መቶ ኮርማዎ
ችን ለካህናት ሰጡ፤ 9 የሌዋውያን አለቆች ኮናን
ያና ወንድሞቹ የሆኑ ሸማዕያና ናታንኤል እንዲ
ሁም ሐሻብያ፥ ይዒኤልና ዮዛባድ ሌዋውያኑ
ለፋሲካ በዓል መሥዋዕት አድርገው የሚያቀርቡ
አቸውን አምስት ሺ የበግና የፍየል ጥቦቶችን እን
ዲሁም አምስት መቶ ኮርማዎችን ሰጡ።
10 ለፋሲካው በዓል የሚሆነው ዝግጅት ከተጠ
ናቀቀ በኋላ ካህናቱና ሌዋውያኑ በንጉሡ ትእዛዝ
መሠረት ቦታ ቦታቸውን ያዙ፤ 11 ለፋሲካውም
በዓል የታረዱትን የበግና የፍየል ጥቦቶች ሌዋው
ያኑ ገፈፉአቸው፤ ካህናቱም ደሙን በመሠዊያው
ላይ ረጩ፤ 12 ለሚቃጠል መሥዋዕት የቀረቡትን
እንስሳት በየቤተሰቡ ለተመደበው ሕዝብ አከፋ
ፈሉ፤ ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት በሙሴ
ሕግ በተሰጠው መመሪያ መሠረት መሥዋዕት
አድርገው እንዲያቀርቡ ነው፤ 13 ሌዋውያኑም
በሕጉ መሠረት የፋሲካውን መሥዋዕት በእሳት
ጠበሱት፤ የተቀደሰውንም ቊርባን በምንቸት፥
በሰታቴና በድስት ቀቅለው ሥጋውን በፍጥነት
ለሕዝቡ አከፋፈሉ፤ 14 ከዚህም በኋላ ሌዋውያኑ
ለራሳቸውና የአሮን ዝርያዎች ለሆኑት ካህናት

35፥4 ፡- 2ዜ.መ. 8፥14 ። 35፥13 ፡- ዘጸ. 12፥8-9 ።

